# እግዚአብሔር የመደበው
# ብቸኛው የማምለኪያ ስፍራ

እንደምን አደራችሁ! ዛሬ ጧት እዚህ በመገኘቴ ደስተኛ ነኝ። በእነዚህ የቆዩ የእምነት መዝሙሮች ዙሪያ በዚህ ታላቅ ኅብረት በመባረካችን፡ ደስ ብሎናል። ይህንን እንወደዋለን። እናንተስ አትወዱትም? የ**አሜን** የሚለው ዝማሬ። እርሱ፡ አሜን ነውና፡ አያችሁ። የመጨረሻውን ቃል የሚናገረው እርሱ ነው።

2 መዝሙሮቹ እየተዘመሩ ሳሉ፡ እዚያ ተቀምጬ ከቀድሞ ጓደኛዬ፡ ከወንድም ብራውን ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። እርሱም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ስለ ምን እየተናገርክ እንደነበር እስከ ትናንትና ድረስ፡ አልገባኝም ነበር” አለኝ። እንዲህ አለ፡ “ሰዎች የምትናገረውን ነገር ብቻ መረዳት ቢችሉ ኖሮ፡” እንዲህ አለ፡ “እያንዳንዱ እንቅፋት ከመንገድ ገለል ይል ነበር” አለ። ይህ ፍጹም ትክክል ነው። ልክ ነው። ፍጹም ትክክል ነው። ልትጨብጡት፡ ልትረዱት ብትችሉ ኖሮ። አያችሁ?

3 ከወዳጄ ከኤርኒ ፋንድለር ጋርም፡ እያወራሁ ነበር። በስልክ መስመር ላይ ያላችሁ እንዳንዶቻችሁ፡ ኤርኒን እንዴት እንደተለወጠና፡ ወደ ጌታ እንዴት እንደመጣ እንደምታስታውሱት እገምታለሁ። እንግሊዝኛ አጥርቶ አይናገርም፡ ቢሆንማ መጥቶ አንድ ቃል እንዲናገር እፈልገው ነበር። የVና የW ፊደላት አጠራር ይደባለቁበታል። እርሱ ሲኖርበት በነበረው፡ በሻዋኖ የነበረ ጊዜ፡ ታስታውሳለህ ወይ ብሎ ጠየቀኝ። አንድ ሉተራን የሆነ ሰው፡ እዚያው ሰብሰባ ላይ ሞተ፡ እዚያው ወንበሩ ላይ ሞቶ ወደቀ። ሁሉም ሰው ጸጥ እንዲል አደረግን። የጌታን ቃል በላዩ ላይ ተናገርን፡ ወደ ሕይወት ተመለሰ፡ ቀጥታም ወደ ስራው ተመለሰ። ኧ-ሃ። ያንን እስካሁን አልረሱትም፡ እንደገና እንድንመለስ ይፈልጋሉ።

4 ዛሬ ጧት እንደተረዳሁት፡ በፈረንሳይ ውስጥ፡ መልእክቱን ወደ-ፈረንሳይ፡ ማለትም አጠቃላይ ፕሮቴስታንት ወደሆነው የፈረንሳይ ክፍል፡ ይዘን እንድንመጣ፡ ከሁለት ሺህ የሚበልጡ ፈረንሳውያን፡ ለበርካታ ቀናት ጾም ላይ ናቸው። ስለዚህ እኛም…

5 አሁን ገና ማበብ እየጀመረ ነው፡ ገና እየጀመረ ነው፡ ስንዴው አሁን ብቅ ብሎ እንዲታይ ቅርፊቱ እየተገለጠ ነው። አያችሁ? ስለዚህ ትሁታን ሁኑ፡ መጸለያችሁን ቀጥሉ። አያችሁ? “እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን፡ ኃይላቸውን ያድሳሉ፡” የሚለውን አስታውሱ።

6 አሁን፡ ይህ… እኔ… በጣም እያረጀሁ ነውና፡ እንዲህ እያሰብኩ ነበር፡ “ሌላ… ሌላ ሪቫይቫል ይኖር ይሆን፡ ሌላ ጊዜስ አያለሁን?” ደግሞም አስታውሱ፡ ከምዕራብ የነጭ ፈረስ ጋላቢ ይመጣል። ይህን መንገድ ዳግመኛ እንጋልበዋለን። በትክክል። ልክ እንደተዘጋጀን። የተሰፋ ቃል ነው፡ አያችሁ።

7 አሁን፡ ለወንድም ሊዮ መናገር እፈልጋለሁ... ትናንት ማታ ወንድሙ እዚህ በመገኘቱ፡ ስለ ወንድም ዉድ ስናገር ነበር። ወንድም ሊዮ፡ አንተና ዛሬ ጧት እዚያ በስልክ መስመር የነበረችው ትንሿ ቡድን ካላችሁ፡ እህት ሜርሲየር፡ አባትሽ እዚህ አለ። ትናንት ማታ አይቼዋለሁ። እዚህ ሕንፃ ውስጥ የሆነ ቦታ ይገኛል፡ ጤንነቱም በጣም የተሟላና በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው።

8 በታበርናክሉ በተፈወሰበት በዚያ ጧት፡ ሊሞቱ የነበሩ፡ ሁለት ከባድ የካንሰር በሽተኞች ነበሩ፡ ሁለቱም ተፈውሰዋል። አባቷም፡ የልብ ህመም አጋጥሞት የነበረው አዛውንት፡ ለእግዚአብሔር ክብር ተፈወሰ። አሁን እዚህ ስብሰባ ውስጥ የሆነ ቦታ አለ። አሁን በሕዝቡ መሃል አላየሁትም፡ ነገር ግን ትናንት ማታ እዚህ ነበር።

9 በምድሪቱ ዙሪያ ላላችሁ ሁሉ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ፥ እዚህ ሽሪቭፖርት በሚገኘው፡ ላይፍ ታበርናክል በተባለው በዚህ ድንቅ ስፍራ፡ ለእሁድ ትምህርት ጢም-ብሎ ከሞላው ሕዝብ ጋር እንድላይ ነን። ታውቃላችሁ፡ እኔ ሽሪቭፖርት ብኖር ኖሮ፡ በማንም ላይ ምንም ክፉ ነገር ለመናገር ሳይሆን፡ ወደ ቤተክርስቲያን የምመጣው፡ ልክ እዚሁ ላይፍ ታበርናክል ነበር። የሐይማኖት ተቋም አይደለም። ላይፍ ታበርናክል፡ ዛሬ፡ ሁሉን አቀፍ ተቋም የሆነ ቤተክርስቲያን ነው። ከሐይማኖት ተቋም የወጡት እኔንና የምሰብከውን ይህን መልእክት ስለተቀበሉ ነው። ወንድሜና ወዳጄ የሆነው፡ ወንድም ጃክ ሙር፡ ከእኔ ጋር ሕብረት ስላደረገ ከሐይማኖት ተቋም አስወጡት። ስለዚህ ዕውቅና ይገባዋል ብዬ አስባለሁ። በትክክል። እግዚአብሔር ይባርከው። በጸሎት እጆቹን ደግፉለት፡ ከእርሱም ጋር እመኑ።

10 አሁን ደግሞ እህት ሙርን፡ የትም አላየኋትም፡ እርሷ፡ አዎ፡ ይኸው ከኋላ፡ ዛሬ ጧት እዚያ ተቀምጣ ልክ እንደ ትንሽ ልጅ ትመስላለች፡ እንዲህ፡ በአዲስ፡ አጊጣ ስትለብስ፡ የፋሲካ ልብስ ይመስላል። እናም... ወንድም ጃክ ራሱ እንኳ አላወቃትም መሰለኝ። አሁን፡ አሁን እህት ሙር!

11 እና ጂንን እና ዶንን፡ ሌሎቹንም ሁሉ በእውነት ናፍቀናቸዋል። እዚህ ካሉት አጋሮች አንዱ የሆነውን... ወንድም ኖላንን፡ በማግኘቴ ደስ ብሎኛል።

12 ትናንትና ወንድም ኤርኒን፡ ያንን **አሜን** የሚለውን መዝሙር ይዘምር እንደሆነ ጠይቄው ነበር። የተቀዳ አለኝና፡ ደጋግሜ በማዳመጥ ብቻ ጨርሼዋለሁ፡ **አሜን።** ለዚህ የሚሆን ድምፅ ያለው ይመስለኛል፥ ከማንኛቸውም ይበልጣል። ትንሿን ጁዲንም፡ አይቻታለሁ፥ ሁለቱ፡ ልክ ወንድምና እህት ይመስላሉ። አይደል እንዴ? እነርሱ ባልና ሚስት ናቸው። እያንዳንዳቸውን ተመልከቱ፡ አያችሁ፡ ፍጹም ይመሳሰላሉ። አያችሁ? በእውነትም በጣም የሚያምሩ ትንንሽ ጥንዶች ናቸው። እነዚህ፡ ታውቃላችሁ፡ እነዚህ... በቅርቡ የወርቁን ደረጃ የወጣው፡ የወንድም ፓልመር ሴት ልጁ እና-እማቹ-ናቸው። እሷ... እርሷ ልጁን ምን ያህል በሥርዓት እንዳሳደገ የሚያሳይ ትልቅ ምስክር ናት። ሌሎች ትዳር የያዙ፡ አገልጋይ ልጆችም አሉት፡ እነዚህም በስራ መስክ ላይ ያሉ ወንጌላውያንና፡ ሌሎችም ናቸው። ስለዚህ ይህ በጣም ግሩም ነው።

13 እህት ፓልመርን አላየኋትም። በእውነት፡ ባያት እንኳ፡ የማውቃት አይመስለኝም። እሷ፡ ምናልባት፡ (በእርግጥ) እዚህ ስብሰባ ውስጥ የሆነ ቦታ

ትኖራለች። እዚያ ወደኋላ በኩል፥ እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህት ፓልመር።

14 ስለ እሱ ባሰብኩ ቁጥር ልቤ ይናወጣል። ወንድም ፓልመር አድማስ እንደተሻገረ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነው፡ እንደሞተ መልእክቱ የደረሰኝ። ፈጽሞ ማመን አልቻልኩም ነበር። ቢሊ ደወለልኝ፡ እናም አንድ ሰው አገኝቶት... አውቀው ነበር። በጣም የምንዋደድ ጓደኛሞች ነበርን፡ ማለፉን ማወቅ፡ በእውነት አናዋጭ ነበር። ነገር ግን ማንነታችን ምንም ይሁን ምን፡ ሁላችንም መሄዳችን አይቀርም፡ አንድ በአንድ መሄዳችን ግድ ነው። ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ አለ፡ “የነገሩን ሁሉ ፍጻሜ እንሰማ፥ እግዚአብሔርን ፍራ ትእዛዛቱንም ጠብቅ፡ ይህ የሰው ሁለንተናዊ ግዴታው ነውና፡” መክብብ 12።

15 አሁን፡ ለዚህ የእሁድ ትምህርት ብዙ ጊዜ የለኝም፡ እንዲሁም ድምፄ ተዘግቷል።

16 ታውቃላችሁ፡ ወንድም ፔሪ ግሪን አንድ መልካም ነገር አድርጓል። ትናንት ማታ፡ እንዲህ ሲል ሰምቶኝ ነበር፡ “የሚረዳኝን ትንሿን ፀጉሬን ረስቼዋለሁ... ” እዚያ ደውሎ አንድ ሰው በአውሮፕላን እንዲልክልኝ ለማድረግ ሞክሮ ነበር። እኔም፡ “አረፍደሃል፡ ድምጼ ቀድመውኑ ተዘግቷል” አልኩት። ለዓመታት መፍትሄ ለማግኘት ስሞክር ነበር፡ ነገር ግን ያንን ሳገኝ፡ ፈወሰኝ። አሁን ግን ስለረሳሁት፡ ድምጼ ትንሽ ተዘግቷል። ስለዚህ በምናገርበት ጊዜ፡ ከቻላችሁ፡ ታገሱኝ።

17 አሁን፡ የሰንበት ትምህርትን ሰንቶቻችሁ ትወዳላችሁ? ኦህ፡ ማይ፡ በትክክል። ልጆቻችሁን ወደዚያ መላክ ጥሩ ነገር ነው። አይደለም፡ ያንን ላስተካክለው፡ ልጆቻችሁን ይዞ **መምጣት** ጥሩ ነገር ነው። በትክክል፡ ልጆቻችሁን ለማምጣት፥ እናንተም አብራችሁ ኑ። የሰንበት ትምህርት በመጀመሪያ እንዴት እንደተጀመረ ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? የት ነው የተጀመረው? በእንግሊዝ። በመጀመሪያ ምን ተብሎ ይጠራ ነበር? **ራግድ ስኩል።** በትክክል፡ “ራግድ ስኩል” ይባል ነበር። የመሰረተውን ሰው ስም አሁን ረስቼዋለሁ። ሰሙ ማን ነበር? [አንድ ሰው፡ “ሮበርት ሬይክስ” አለ።—አርታዒ።] ልክ ነው፡ በትክክል። እነዚያን ትንንሽ ልጆች ከመንገድ ላይ ሰበሰባቸው (የተቀዳደደ ልብስ የለበሱ፡ የሚሄዱበት ቦታ የሌላቸውና፡ በጣም መጥፎ ሁኔታ ላይ የነበሩትን)፡ ወደ ውስጥ በማስገባትም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሊሰጣቸው ጀመረ። ዛሬ ደግሞ፡ እያደገ መጥቶ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ካሉ ታላላቅ ሥርዓቶች አንዱ ለመሆን በቅቷል፡ የሰንበት ትምህርት። መሄድ ጥሩ ነው። መምጣታችሁን አረጋግጡ፡ ልጆቻችሁንም አምጡ። እዚህ ያለው ታበርናክል መምህራን፡ የተሟሉ ክፍሎች፡ ለእድሜ ደረጃ የሚመጥኑ ነገሮችና፡ የመሳሰሉት አሉት ብዬ አስባለሁ። አሁን ወደ ክርስቶስ እየመጣችሁ ያላችሁ አዳዲስ አማኞች፡ መልእክቱን በሚገባ ተከተሉ፥ እዚህ ላይፍ ታበርናክል ኑ፡ እነርሱም መልካም ያደርጉላችኋል።

18 አሁን፡ ዛሬ ማታ የጥንቱ-ዓይነት የጸሎት መሰመር ይኖረናል። ወንድም ጃክና ወንድም ብራውን፡ ድሮ እናደርገው እንደነበረው ለታመሙት ብቻ እንጸልያለን።

19 ወንድም ብራውን እነዚያን የጸሎት ካርዶች ለማደል ሲሞክር ሳየው አስታውሳለሁ፡ ራሱም አገልጋይ እንደመሆኑ፡ በዚያን ጊዜ፡ በአንድ ድርጅት

ውስጥ ሆኖ፡ እነርሱ፡ እንዴት ጫና ያሳድሩበት እንደነበር፡ ታውቃላችሁ፡ “እ—እኔ በዚህ ነገር ወንድምህ ነኝ፡” ታውቃላችሁ፡ “ወደዚያ እንድወጣ ማድረግ አለብህ።” ኦህ፡ በእርግጥ ከባድ ጊዜ አሳልፏል፡ ነገር ግን ሊሆን በሚችለው መጠን እውነተኛ ሆኖ ጸንቷል። ወንድም ብራውን መልካም ሰው ነው። ስለዚህም እንወደዋለን።

20 ሁላችንም፡ ሦስታችንም፡ ወደ እርጅና፡ ወደ መጨረሻው ሰንጠጋ፡ እያዘገምን ስንሄድ አያለሁ። እውነት እንደሆነ የምናውቀውን ያንን ታላቅ ነገር በውስጣችን ባናኖር ኖሮ፡ በጣም የሚያሳዝን ነገር ይሆን ነበር። አሁን ልክ ከእነዚህ ቀናት በአንዱ ወደኋላ ለመመለስ፡ እንደገና ወደ ወጣትነት ጊዜያችን ለመመለስ ዝግጁ እየሆንን ነው፡ ዳግም ላለማረጅ... አካላችን ተለውጦ፡ በእርሱ መልክ ተመስሎ ለመቆም ነው። “ይህ የምንኖርበት ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስ፡ አስቀድሞ የተዘጋጀ ሌላ አለና።”

21 የሚያስመሰግነው ነገር፡ ውድ ወዳጆች ሆይ፡ ውዱ ጌታ ኢየሱስ... እውነቱን እንድነግራችሁ ለምታምኑኝ፥ ውዱ ጌታ ኢየሱስ፡ አንድ ቀን ጧት በሰምንት ሰዓት ገደማ፡ ያችን አገር እንዳያት ፈቀደልኝ። አሁን፡ ራ—ራእይ አልነበረም፡ ወይም፡ እንደዛ ማለት አልፈልግም። ምንም ይሁን ምን፡ ልክ አሁን እዚህ ለእናንተ እየተናገርኩ እንዳለሁት ያህል እውነተኛ ነበር። አሁን፡ የእነዚያን ሰዎች ፊቶች አየሁ፡ ነገር ግን ላውቃቸው አልቻልኩም፡ ተመልሰው ወጣት ሆነው ነበር። ልክ እንደ... እጆቻቸውን ሰይዝና ሌሎችንም ነገሮች ሳደርግ ነበር። ልክ ያን ያህል እውነተኛ...

22 ያም ረድቶኛል፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ሲሞት፡ ነፍሱ ብቻ ትሄዳለች የሚል አመለካከት ነበረኝ። ነገር ግን ያንን ለእኔ ሲጠቅሰልኝ፡ “ይህ የምንኖርበት ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስ... አስቀድሞ የተዘጋጀልን ሌላ አለን” የሚለውን። አያችሁ? ፍጹምነትን ለማምጣት፡ ሁሉንም ነገር በሦስትነት ማግኘት አለብን። አያችሁ? እዚህ ያለው አንደኛው አካል አለ፡ ቀጥሎም እዚያ ያለ አካል ነው ያም ሰ—ሰማያዊው አካል ነው፡ ከዚያም ደግሞ በትንሣኤ ጊዜ የሚኖረው የከበረው አካል። አያችሁ፡ ያ ሙሉ ያደርገዋል። አያችሁ? ስለዚህ እሱ... እሱ ተረት አይደለም፡ ሃሳብ አይደለም፡ መንፈስም አይደለም። ልክ እንደ እናንተው ያለ ወንድና ሴት ነው፡ በትክክል።

23 ከዛም፡ ከዓመታት በፊት፡ የጠፉ ነፍሳት የሚገኙበትን ሰፍራዎች አየሁ፡ እዚያም ነበርኩ። እነግራችኋለሁ፡ ወዳጆቼ፡ እንደ አንድ አዛውንት፡ ይህንን ላሳምናችሁ፡ ዛሬ ጧት በመላው አገሪቱ ያላችሁ፡ ያንን ቦታ ለማየት ፈጽሞ አትመኙ። በምንም መንገድ እኔ... ብሩሽ የያዝኩ ሰዓሊ እንኳ ብሆን ሰዕሉን ልሰለው አልችልም ነበር። እንደ አንድ አገልጋይ፡ ልገልጽላችሁ አልችልም። ገሃነም የሚቃጠል ሰፍራ ስለመሆኑ ከተነገረው፡ ከአሰፈሪነቱ፡ አንድ ሚሊዮን ጊዜ የከፋ ነው።

24 ሰማይ፡ ወይም፡ ይሄ ቦታ፡ የትም ይሁን የት፡ ምን ብዬ እንደምጠራው አላውቅም። እርሱ እዚያ “በመሠዊያው ሥር ያሉ ነፍሳት” ብሎ ጠርቶታል። ነገር ግን በሆነው ጊዜ፡ እኔ ፈጽሞ... ያ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ለማስረዳት የሚቻልበት መንገድ የለም። እዚያ... አሁን፡ ቃሌን ብቻ ማመን አለባችሁ፡ እኔ እንዲሁ ሰው ነኝና። አያችሁ? ነገር ግን ልክ እንደነገርኳችሁ ሁልጊዜም

የሚፈጸሙት እነዚህ ራእዮች፡ እያንዳንዳቸው እውነት እንደነበሩ እንደምታውቁት ሁሉ፡ **ያም** እውነት ነው። ምንም ብታደርጉ፡ ሌላውን ነገር ሁሉ ብታጡ እንኳ (ጤንነት፡ ጥንካሬ፡ የዓይናችሁን ብርሃን፡ ምንም ይሁን ምን)፡ ያ እንዳያመልጣችሁ። ከእርሱ ጋር ሊወዳደር የሚችል ምንም ነገር የለም። እሱ... እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስጥ ያንን ሊገልጽ የሚችል፡ ም—ምንም ቃል የለም። "ፍጹም" ብትሉ፡ ከዚያም በላይ ነው፥ "ድንቅ፡" ከ—ከዚያም በላይ ነው፥ "የላቀ፡"... እ—እሱን ሊገልጹት የሚችሉ እኔ የማውቃቸው ቃላት የሉም፡ ምክንያቱም በጣም... ከዚያም፡ ስታስቡት፡ ያ ገና መጨረሻው አይደለም። "እኔ ወደዚህ ለመምጣት አስፈራኝ እንዴ፡" ብዬ አሰብኩ?

25 እኔም፡ "ትበላላችሁ" አልኳቸው?

26 እንዲህ አለ፡ "እዚህ አይደለም። እዚህ አንበላም፡ ነገር ግን ወደ ምድር ስንመለስ የምንበላበትን አካል እንቀበላለን።"

27 እንግዲህ፡ ልዳስሳቸው እችል ነበር። ልክ **እንደዛ** ነበሩ። አያችሁ? እነርሱ... እኔም እንዲህ አልኩ፡ "ታዲያ፡ እናንተ... " ኦህ፡ አዎን፡ አካል አላቸው። ዝም ብሎ ተረት አይደለም፡ አካል ነው። እርስ በርሳችን እንተዋወቃለን። ሁሉም ያውቁኝ ነበር፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩት፡ እያቀፉኝ ነበር።

28 እኔም፡ "እንግዲያውስ፡ ወደዚህ ያመጣኝን እርሱን ማየት እፈልጋለሁ" አልኩ።

29 እርሱም፡ "አሁን እርሱን ማየት አትችልም፡ መጠበቅ አለብህ" አለኝ።

30 እኔም፡ "ለምን ወደዚህ... አመጣኸኝ" አልኩ?

31 እንዲህ አለ፡ "በሕይወት ዘመንህ መሪ ነበርክ።"

32 እኔም፡ "እነዚህ ሁሉ ብራንሃሞች ናቸው ማለትህ ነው" አልኩኝ?

33 እርሱም፡ "አይደለም! እነዚህ አንተ ወደ ክርስቶስ ያመጣሃቸው ናቸው" አለኝ። አያችሁ?

34 ዙሪያዬን ተመለከትኩ፡ ፊቶቻቸውን ሳየው፡ እነዚያ ሁሉ አስቸጋሪ ሌሊቶችና፡ ፈተናዎች፡ አለፉ። አንዲት ወጣት ሴት ወደ እኔ ሮጣ መጣች፡ እጅግ ውብ ከሆኑ ሴቶች አንዷ ነበረች፡ እጆቿንም በአንገቴ ዙሪያ ጠምጥማ አቅፋኝ፡ "ውድ ወንድሜ፡" አለችኝ። እሷ አልፋ ስትሄድ... አሁን፡ እሷ ሴት ነበረች። ስለዚህ... ነገር ግን እዚያ ውስጥ፡ ፈጽሞ ኃጢአት አይኖርም። አያችሁ፡ እዚያ ዕጢዎቻችን ተለውጠዋል። እዚያ ከእንግዲህ ወዲህ፡ ልጆችን አያፈሩም። አያችሁ? አያችሁ፡ ሁሉም አንድ ዓይነት ነው።

35 ልዩነት የሚያመጣው፡ ስሜቱ ነው። በወለል ላይ መጨፈርን የማላምንበት ምክንያት ይሄው ነው። ማንም ሰው... እኔ፡ በእግዚአብሔርና በመጽሐፍ ቅዱሴ ፊት፡ ከልጅነቴ ጀምሮ፡ በወጣትነት ጊዜዬ ሁሉ፡ ንጹሕ ሆኜ ኖሬያለሁ። አብሬያት ከወጣኋት ከማንኛዋም ሴት ጋር፡ ያለምንም ችግር ቀጥታ ወደ ፍርድ አደባባይ አብሬያት መሄድ እችላለሁ። አያችሁ? ነገር ግን ማንኛውም ሰው፡ ማንኛውም ሰው ብትሆን ግድ የለኝም፡ አንዲት ሴት (በሴትነት ተፈጥሮዋ) ወደ አንተ ጠጋ ብላ እንድታቅፍህ ብትፈቅድላት፥ ትክክለኛ ጤናማ ወንድ ከሆንክ፡ የሆነ ስሜት መፈጠሩ አይቀርም። ነገር ግን እዚያ ያ ስሜት አልነበረም፥ ዕጢዎች

የሉም። ሁላችሁም ተመሳሳይ ናችሁ። አያችሁ? ንጹሕ፡ ያልተበረዘ የእህትነትና የወንድምነት ፍቅር ብቻ ነው፡ የራስህን ትንሿን ልጅህን... እንኳ ከምታቅፍበት ጊዜ... የበለጠ ነው። አያችሁ? የገዛ ልጅህ፡ ነገር ግን እርሷ የተፈጠረችው... እርሷ ሴት ናት አንተ ደግሞ ወንድ ነህ። አያችሁ፡ የሆነ ነገር ሊፈጥር ይችላል፥ ነገር ግን እዚያ አይችልም፡ ኃጢአት አብቅቷል፡ ሁሉም አልፏል። አያችሁ? እውነተኛ... እውነተኛና፡ ቅዱስ ፍቅር ብቻ ነው።

36 ያቺንም ሴት ተመለከትኳት። እዚያ... በሚሊዮን የሚቆጠሩ ይመስሉ ነበር፡ ሁሉም ረጅም ጸጉር ነበራቸው፡ እንዲሁም ወደ ታች የሚወርድ ነጭ ልብስ ለብሰው ነበር። እ—እና ሲያነጋግረኝ የነበረው፡ "አላወቅካትም እንዴ፡" አለኝ?

37 እኔም፡ "አላወቅኳትም" አልኩኝ።

38 እርሱም፡ "ወደ ክርስቶስ ስትመራት በዘጠናዎቹ ዕድሜ ውስጥ ነበረች" አለኝ።

39 "ድንቅ ጸጋ፡ ድምፁ እንዴት ይጣፍጣል።" አያችሁ? ያ ምን እንደሆነ ፈጽሞ ለማስረዳት የሚቻልበት መንገድ የለም። የምታምኑኝ ከሆነ ቃሌን ብቻ ተቀበሉ። ከኋላችሁ ያለውን የዓለምን ድልድይ ሁሉ... ማቃጠላችሁን አረጋግጡ።

40 ቤተ ክርስቲያን መልእክቱን መስማት፡ እንዲሁም መረዳት እየጀመረች እንደሆነ አምናለሁ። ነገር ግን፡ ወዳጆቼ፡ አዳምጡ፡ በልጅ ፊት መታየት አለብን፡ መብሰል አለብን። እ—እምነታችን ገና አልጎመራም። በእውቀት ደረጃ እግዚአብሔር የሰጠንን መልእክት እየሰማን፡ ያሳየንንም ምልክቶች እያየን ነው፡ መኖሩንም፡ በመጽሐፍ ቅዱስም እያረጋገጥነው ነው፡ ነገር ግን፡ ኦህ፡ ቤተክርስቲያን እስክትጎመራ ድረስ፡ ታውቃላችሁ፡ በመንፈስም እስክትጣፍጥና ወደ ውስጥዋ እስኪሰርጽ ድረስ በእርሱ ፊት መታየት እንዴት ያስፈልጋታል። አንዳንድ ጊዜ መልእክቱን ስትናገሩ፡ ጠንከር ትላላችሁ፡ ልክ እንደዚያ ሰብራችሁ መግባት ይኖርባችኋል፡ ምክንያቱም ሚስማሩ አጥብቆ እንዲይዝ ጫፉን ማጠፍ ስላለባችሁ ነው። ነገር ግን ቤተክርስቲያን አንዴ ስትቀበለው፡ የተመረጡት ተጠርተው ሲለዩ፡ ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት፡ ንጥቀቷን ስታደርግ ልክ እዚያ እንደነበሩት ሰዎች ዓይነት እንደሚሆን አውቃለሁ።

41 ዛሬ ጧት ስለ **ንጥቀት** ልናገር አስቤ ነበር፡ ነገር ግን ይህንን ለማድረግ የሚያስችል በቂ ድምፅ የለኝም፡ ስለዚህ በዚህ ርዕስ፡ **እግዚአብሔር የመደበው ብቸኛው የማምለኪያ ስፍራ** በሚለው ርዕስ ላይ ስናገር ለጥቂት ጊዜ ታገሱኝ።

42 አሁን፡ ይህ በጣም ትልቅ ርዕስ ነው። ስለዚህ አሁን እንጸልይ። ዛሬ ጧት በየአገሪቱ ያላችሁ፡ የትም ብትሆኑ፡ ለጥቂት ጊዜያት አንገታችሁን ዝቅ አድርጉ። አሁን በእውነት ቅን ሁኑ፡ ወደ እግዚአብሔር ቃል እየቀረብን ነው፡ ይህም በፊደል መልክ የሆነው እግዚአብሔር ነው።

43 የዚህ መጽሐፍ ታላቅ ደራሲ፡ ደራሲው እንደተናገረው፡ "ዘሪው የዘራው፡" "ዘር ነው፡" ተብለን ተምረናል። አሁን፡ ዘር ትክክለኛ ዓይነት መሬት ላይ ከወደቀ እንደሚያድግ እናውቃለን። ስለዚህ፡ አባት ሆይ፡ በዚህ ጧት እኛህንና አሜኬላን፡ አለማመንን፡ ተጠራጣሪ ሀሳቦችንም ሁሉ ከልባችን ታወጣለህን፥ ይህም የእግዚአብሔር ህዝብ መሆን እንድንችል የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ውኃ እየጠጣ በልባችን ውስጥ በነፃነት ያድግ ዘንድ ነው። አባት ሆይ፡

ይሁንልን። የልባችን ፍላጎት ይሄው ነው። ይህንን ላወቅን ለእኛ ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን በመላው ሀገሪቱ ላሉ ሌሎችም፡ የእያንዳንዳቸው ልብ በፍቅርና በገርነት እየተቀጣጠለ፡ የጠፉውን ወንድም፡ የጠፉችውንም እህት ለማትረፍ የሚሄዱ ይኖሩ ዘንድ ነው። አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ይህ ይሁንልን። ሙሉ በሙሉ ወደ አንተ እየተመለከትን ነው፡ አንተ መሪያችንና ጌታችን ነህና። ስለዚህ ዛሬ በቃልህ እንድትመራን፡ ከበረከትህም እንድትሰጠን እንጸልያለን። በጸጋህና በስምህ እንለምንሃለን። አሜን።

44 አሁን፡ ወደ ሀሳባችን እንምጣ... የቃሉን ክፍል ለማስያዝ ያህል ብቻ፡ ከብሉይ ኪዳን፡ ከዘዳግም መጽሐፍ ላነብ እፈልጋለሁ። ከወንድም ቬይል ጋር ቁርስ በልቼ ከተመለስኩ በኋላ በፍጥነት የጻፍኳቸው ጥቂት ማስታወሻዎች አሉኝ።

45 በዚያ ሆቴል... በቀደም ምሽት በዚያ ሬስቶራንት የራት ሂሳባችንን የከፈለልንን፡ ያንን ሰው የ—የማመስግንበት አጋጣሚ አላገኘሁም። ባለቤቴ እኔና ትንሿ ልጄ እዚያ ነበርን፡ ሂሳብ ልከፍል ስሄድ፡ አንድ ሰው ከፍሎት ነበር። ማንም ይሁን ማን፡ አመሰግንሃለሁ። "በወንበሩ ጫፍ ላይ የተቀመጠው ሰው ነው፡" አሉኝ። በእርግጥ እዚያ ውስጥ እኛ የምናውቃቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ። አሁን፡ እኔ... ኪካፑ የሚመስል ስም ያለው፡ የሆነ እንደዚያ ዓይነት ስም ያለው፡ እዚህ ውጭ ያለው፡ የነበርንበት ሬስቶራንት ነው። ያንን ላደረግኸው ሰው ማንም ሁን ማን፡ አመሰግንሃለሁ። እያንዳንዳችሁን፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

46 እንግዲህ፡ በዘዳግም ምዕራፍ 16 ላይ፡ የፋሲካው በዓል ነው። ስለዚህ የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ጥቅሶች እናንብብ፡ የመጀመሪያዎቹን አራት ወይም አምስት፡ ስድስት ቁጥሮችን እናነባለን።

> **በአቢብ ወር፡ እምላክህ እግዚአብሔር...** (ይህም "ሚያዝያ" ማለት ነው።)... **በሌሊት ከግብፅ ስላወጣህ፥ የአቢብን ወር** ጠብቅ **የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ፋሲካ አድርግበት።**
>
> **አምላክህ እግዚአብሔር በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ በመረጠው ስፍራ፡ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ከበግና ከላም መንጋ ፋሲካ ሠዋ**...
>
> በዚያም **ውስጥ ያልቦካውን እንጀራ** ትበላለህ፥ **ሰባት ቀን ያልቦካ ቂጣ—ቂጣ ትበላለህ፡ ይህም፡... ከግብፅ አገር በችኰላ ስለ ወጣህ፥... በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ከግብፅ ምድር የ**ወጣህ**በትን ቀ—ቀን ታስታውሳለህ።**
>
> **ሰባት ቀንም... በአገርህ ዳርቻ ሁሉ** እርሾ **አይታይም፥ በመጀመሪያው ቀን ማታ ከሠዋኸው፡ ሥጋም፡ እስከ ነገ ድረስ ምንም አይደር።**
>
> **አምላክህ እግዚአብሔር ከሰጠህ ከአገርህ ደጆች፡ በማንኛይቱም ፋሲካን ትሠዋ ዘንድ አይገባህም፥**
>
> **ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ስሙ ይጠራበት ዘንድ በመረጠው በዚያ ስፍራ፡ ከግብፅ በወጣህበት** ወራት፡ **ፀሐይ ሲገባ፡ ማታ ፋሲካን ሠዋ።**

እንግዲህ ጌታ በቃሉ ንባብ ላይ በረከቱን ይጨምር።

47 አሁን፡ ድምፅ ማጉያዎቹ ብዥታ አላቸው እንዴ? ትላንት ማታ እንደዚያ እንደነበሩ ሰምቻለሁ። በየቦታው፡ በደንብ ይሰማችኋል? አይሰማችሁም። [ወንድም ብራንሃም ማይክሮፎኑን አስተካከለ—አርታዒ።] አሁንስ ይሻላል? ማይክሮፎኖቹን እንደዚህ ዝቅ አድርጌ ሰናገር፡ ይሻላል? ድምፄን ትንሽ ዘግቶኛል፡ ስለዚህ ዛሬ ጠዋት ለዚያ ብዬ ጠጋ ብዬ ቆሜአለሁ፡ ወንድም ፔሪ ድምፁን ወደ ውጭ እ—እንደሚያሰማው ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን በደንብ ይሰማችኋል? ያስተካከሉት ይመስለኛል። መልካም።

48 አሁን፡ ሰፍ-... ዛሬ ጠዋት ልናገርበት የምፈልገው ነገር አምላኪው ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኝ የሚችልበት አንድ የእግዚአብሔር ሰፍራ ብቻ እንዳለ ነው፡ አንድ ሰፍራ ብቻ። በዘመናት ሁሉ ብዙዎች ይህንን የተሰወረ የእግዚአብሔር ሰፍራ ሲፈልጉ ቆይተዋል፡ በዘመናት ሁሉ። ኢዮብ እንኳ እርሱ የት እንደሚኖር ማወቅ ፈልጎ ነበር፡ “ወደ ቤቱ ሄጄ በሩን ማንኳኳት ብቻ ብችል ኖሮ።” ኢዮብ የእግዚአብሔርን ማደሪያ ሰፍራ ማግኘት ፈልጎ ነበር፡ ምክንያቱም በዚያ እግዚአብሔርና ቤተሰቡ በአንድነት ይመለካሉና።

49 ልክ እንደ ትላንትናው፡ በትላንትናው ጠዋት መልእክት ላይ፡ አንድ ሰው ከልብ ቅንነት በሆነ አምልኮ፡ እግዚአብሔርን በከንቱ ሊያመልክ የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለ አይተናል። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለእኛ አዘጋጅቶልናል፡ ነገር ግን ዋናው ነገር፡ እነርሱ የት እንዳሉ ፈልገን ማግኘት አለብን። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲመረምርና፡ በ—በጊዜውም አለጊዜውም ዝግጁ እንዲሆን፡ በ—በ—በውስጡ ስላለው ተስፋ ቃል ወይም... መልስ ለመስጠት የተዘጋጀ እንዲሆን ነግሮታል።

50 አሁን፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች እዚያ ውስጥ አሉ። እኛም... አንዳንድ ጊዜ ወደ ሽሪቭፖርት መጥቼ ልክ በየማታው ሠላሳ ደቂቃ እየወሰድን ለሁለት ወይም ሦስት ሳምንታት ያህል ትምህርት ብቻ ብንማር ደስ ይለኛል፡ አያችሁ፡ ቃሉ ውስጥ ብቻ መቆየት፡ እነዚህ የተሰወሩ መንገዶች፡ አያችሁ፡ እንዴት መግባት እንዳለብን ማወቅ እንድንችል ነው። እናንተ ብቻ ተመልከቱ፡ የእግዚአብሔርን መመሪያ ተከተሉ፡ ለእያንዳንዱ በር አንድ ቁልፍ ብቻ ነው ያለው። በትክክል። ሌላ ምንም ቁልፍ የለም፡ ምንም ያህል ትክክለኛውን ቢመስልም፡ እግዚአብሔር ስከለተን ቁልፍ የለውም፡ ያለው አንድ ቁልፍ ብቻ ነው። አሁንም፡ ያ ቁልፍ ሊኖራችሁ ይገባል፡ አለበለዚያ በሩ አይከፈትም። ምንም ያህል ቅን ብትሆኑም፡ አሁንም ያንን በር ልትከፍቱት አትችሉም።

51 አሁን፡ ትላንትና በነበረው የቁርስ ሰዓት፡ በቀደም ጠዋት የነበራችሁት ስንቶቻችሁ ናችሁ? ጥሩ፡ አብዛኞቻችሁ፡ ቢያንስ ዘጠና በመቶ የሚሆናችሁ፡ ወይም ከዚያ በላይ የነበራችሁ ይመስለኛል። አሁን ለምናገረው ነገር፡ መነሻ ለማድረግ፡ ዳዊት (በእግዚአብሔር የተቀባ) የተቀባ ንጉሥ ነበር፡ ይኸውም የተቀባው ከሆነው ከጌታ ኢየሱስ (ይህም እግዚአብሔር ከሆነው) በስተቀር፡ እስራኤል ካገኘቻቸው ነገሥታት ሁሉ ታላቁ ንጉሥ ነበር። ዳዊት የእርሱ ልጅ ነው፡ ማለትም፡ በዘር ሐረግ ሲታይ፡ ኢየሱስ የዳዊት ልጅ ነበር። ልዑል ሁልጊዜ የንጉሥን ዙፋን እንደሚወርስ፡ እርሱም እ—እንደ ወራሽ በ—በዳዊት ዙፋን ላይ ሊቀመጥ ነው።

52 አሁን፡ አስተውሉ፡ ዳዊት የተቀባ ሆኖ ሳለ፡ በዚያ ባለው ቅባት እንኳ፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ወጣ፡ ሕዝቡም ሁሉ፡ የመጽሐፍ ቅዱስን መንገድ ወይም የዚህን መገለጥ ቁልፍ ሳይዙ፡ ሁሉም፡ አንድላይ፡ የተቀቡ ሆነው፡ ፍጹም ትክክል ለሚመስል ነገር ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል ወደ እግዚአብሔር ቤት ለመመለስ፥ ሁሉም በአንድነት ሆነው እየጮሁና እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ነበር። ነገር ግን ዳዊት ንጉሥ እንጂ፡ ነቢይ አልነበረም። አያችሁ? እርሱ... ያንን የሚያደርግ ነቢይ በምድሪቱ ላይ ነበረ፡ ትክክለኛውን ቁልፍ ስላልተጠቀሙ እግዚአብሔር ያንን እንቅስቃሴ ሁሉ አልተቀበለውም። በሩ አልተከፈተም። አሁንም ያንን ማስታወስና፡ በአእምሯችን ልንይዘው ይገባል። ነገሩ... የእግዚአብሔር የሆነው ነገር ሁሉ፡ ሊደረግ የሚችልበት አንድ የተወሰነ መንገድ አለው፡ ያም ነገሩን ይቋጨዋል። አሁን፡ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝባት አንድ የተወሰነች ቤተክርስቲያን አለችው፡ በዚያች ቤተክርስቲያን ውስጥ ይቀበላችኋል እንጂ በሌላ በማንኛውም ቤተክርስቲያን ውስጥ አይቀበላችሁም።

53 ይህንን ያልኩት ብዙ ጊዜ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ስለሚረዱኝ ነው፡ ሰዎች እንዲህ ሲሉ...

እኔም፡ "አንተ ክርስቲያን ነህ" ስል?

"እኔ ባፕቲስት ነኝ" ይላሉ።

"አንተ ክርስቲያን ነህ? "

"እኔ ሜቶዲስት ነኝ።"

"አንተ ክርስቲያን ነህ? "

"እኔ ጴንጤቆስጤ ነኝ።"

54 አሁን፡ አያችሁ፡ ያ ለእግዚአብሔር ምንም ትርጉም አይሰጠውም። በተሳሳተ ቁልፍ በሩን ለመክፈት እየጎረጎራችሁ ነው። ነገር ግን ትክክለኛ ቁልፍ አለ፡ እግዚአብሔር... እግዚአብሔር እንደ ሜቶዲስት፡ ወይም እንደ ባፕቲስት፡ ወይም እንደ ጴንጤቆስጤ፡ ወይም እንደ ሌላ የትኛውም የሐይማኖት ተቋም ሆኖ ሊገናኛችሁ ቃል አልገባም። የሐይማኖት ተቋማትን ከግምት ውስጥ እንኳ አያስገባም፡ እነርሱ እርሱን የሚቃወሙ ናቸው።

55 በዚያ ረጅም መልእክት ላይ፡ በቅርቡ በታበርናክሉ አቀርበዋለሁ። ከዚያም ወንድም ጃክ ይሰማዋል፡ ከዚያም ስለ ጉዳዩ ምን ማድረግ እንደምትፈልጉ ማየት ትችላላችሁ፡ ምክንያቱም በካሴት ስለሚቀዳ ነው።

56 አሁን፡ ሰዎች እግዚአብሔር በሥነመለኮት ትምህርታቸው መሠረት ብቻ ሊያገኛቸው ግዴታ ያለበት ይመስል ያደርጋሉ። አሁን፡ ሰዎች እንደዚህ ይሆናሉ። እርስ በርሳቸው እንኳ ሕብረት አያደርጉም። የጴንጤቆስጤ የሥላሴ አማኞች ከዋንነስ አማኞች ጋር ሕብረት አያደርጉም፡ የዋንነስ አማኞችም ከሥላሴ አማኞች ጋር ሕብረት አያደርጉም። ሜቶዲስት ከባፕቲስት ጋር ሕብረት አያደርግም፡ ምክንያቱም አንደኛው ሕግ አጥባቂ ሌላኛው ደግሞ ካልቪኒስት ስለሆነ ነው፡ ስለዚህ ምንም ዓይነት ሕብረት የላቸውም። የሰዎችንም አእምሮ ክፉኛ ስለጠመዘዙት እርስ በርሳቸው እንኳ ጠላት እስኪሆኑ ድረስ ደርሰዋል።

57 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ በአንድ ሆስፒታል ክፍል ውስጥ፡ ለመጸለይ ሄጄ ነበር። እዚያ በጠና ታማ የተኛች አንዲት ሴት ነበረች፡ ቀዶ ጥገና ልታደርግ ነበር፡ እንደምትሞትም ይጠበቅ ነበር። እዚያ የተኛች ሌላ ሴት ነበረች (እኔ የተጠራሁት ለእርሷ ለመጸለይ ነበር።)፡ እኔም፡ "ለጥቂት ጊዜ ብጸልይ ቅር ይልሻል" አልኳት?

58 እርሷም፡ "ያንን መጋረጃ ዝጋው" አለች!

59 እኔም፡ "ይቅርታ፡" እንዲህ አልኳት፡ "ጸሎት ለማድረግ ልጠይቅ ብዬ ብቻ ነው" አልኳት።

60 እርሷም፡ "ያንን መጋረጃ ዝጋው" አለች!

61 እኔም፡ "እሺ፡ እመቤቴ" አልኳት። እርሷና ልጇ እዚያ ተቀምጠው ነበር፡ ልጇ ልክ የተለመደው ዘመናዊ **ሪኪ** ገጽታ ነበረው። እኔም፡ "ደህና፡ ክርስቲያን አይደለሽም እንዴ" አልኳት?

62 እርሷም፡ "እኛ ሜቶዲስት ነን" አለች!

63 እኔም፡ "እንግዲህ፡ ያንን አልጠየቅሁሽም፡ 'ክርስቲያን' እንደሆንሽ ነው የጠየቅሁሽ" አልኳት። አያችሁ?

64 ስለዚህም እርሷ፡ "ያንን መጋረጃ ዝጋው" አለች!

65 አያችሁ፡ ሜቶዲስት ያልሆነ ሰው በሞት አፋፍ ላይ ላለች ሴት ጸሎት ሊያደርግ ስለነበር ነው፡ እርሷም ራሷ በዚያው ሁኔታ ላይ ነበረች። ነገር ግን ከእርሷ ድርጅት ጋር የተገናኘ ስላልነበር፡ ፈጽሞ ልትሰማው ወይም ከነገሩ ጋር ምንም ዓይነት ንክኪ እንዲኖራት አልፈለገችም። ይህ ፈሪሳዊነት ካልሆነ፡ እኔ ፈሪሳዊ አይቼ አላውቅም!

66 **የእባቡን መንገድ** አስክትሰሙ ድረስ ጠብቁ። ሃህ። መልካም። አሁን፡ የእነርሱ የሐይማኖት ተቋም ብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው እንደሆነ ያስባሉ፥ "ሜቶዲስት፡ ወ—ወይም ባፕቲስት፡ ወይም የሥላሴ፡ ወይም ዋንነስ ካልሆንክ በቀር፡ እግዚአብሔር አይሰማህም፡" ወይም ሌላ እንደዚያ ያለ ነገር። ያ ስህተት ነው!

67 ዓላማዬም ያ ነው፥ ነገር ግን በ—በሰዎች አእምሮና ልብ ውስጥ ትክክለኛ ለመሆን እንደዚህ ያለ ፍላጎት ካለ... ያች ሴት ያንን ያደረገችው... ወይም ሌላ ማንም ሰው ለክፋት ብሎ ነው ብዬ አላምንም። አንድ ሜቶዲስት ስህተት መሆኑን ቢያውቅ—ኖሮ ተነስቶ ስለ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን አይሟገትም ነበር ሰውየው ትክክል እንደሆነ ያሰባል። በጴንጤቆስጤ ውስጥ ያለ የሥላሴ አማኝ የዋንነስ አማኙን፡ ወይም የዋንነስ አማኙ፡ የሥላሴ አማኙን የሚያወግዘው፡ የተለየ መሆን ስለፈለገ ነው፡ ብዬ አላምንም፡ ትክክል እንደሆነ ስለሚያስብ ነው፡ የእርሱን ሃሳብ ማክበር አለባችሁ። ታውቃላችሁ፡ ብርድልብሱ በሁለቱም በኩል ይሳባል። ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ፡ በአንድ ወንድ ወይም ሴት ልብ ውስጥ "ትክክል" ነው ብለው ያመኑት አንዳች ነገር ካለ፡ ትክክል የሆነበት አንዳች ስፍራ መኖር አለበት። ብዙ ጊዜ እንደምለው፡ "ጥልቅ ወደ ጥልቅ ሲጠራ፡ ለዚያ ጥሪ ምላሽ የሚሰጥ ሌላ ጥልቅ መኖር አለበት።"

68 ታውቃላችሁ፡ የባሕር አንበሳ በአንድ ወቅት በ—በባህሩ ዳርቻ ላይ፡ በእግሮች ይራመድ እ—እንደነበር ይነገራል። ነገር ግን አሁን እግሮች የሉትም፡

እግሮቹ ወደ መቅዘፊያዎች ተለውጠዋል ምክንያቱም እሱ... ከየብስ ፀጉራም-እንስሳ ሆኖ፡ ወደ ባህር ሲገባ፡ መቅዘፊያዎቹ ስላስፈለጉት ነው፥ ከመራመዱ ይልቅ መዋኘቱ ስለሚበልጥ፡ ተፈጥሮ ከእግሮች ይልቅ መቅዘፊያዎችን አበጀችለት።

69 አሁን ወደ ደቡብ ዋልታ የሄደውን የዚህን ታላቅ ሰው ስም ትዝ አይለኝም። ስሙ ማን ነበር? በርድ። በዚያ ጉዞ ላይ፡ ለአንዳንድ ከብቶች ካፖርት አሠርቶ እንደነበር ይናገራሉ፥ ከብቶቹንም የወሰደው ለወተት ነበር። ከብቶቹም በብርድ እንዳይሞቱ ለመጠበቅ የፀጉር ካፖርቶችን አዘጋጀላቸው። እዚያ ሲደርስ ግን፡ ምንም ዓይነት የፀጉር ካፖርት አላስፈለጋቸውም፥ ተፈጥሮ አብቅሎላቸው ነበርና። አያችሁ? ለምን? በአሳ ጀርባ ላይ ክንፍ ከመኖሩ በፊት፡ የሚዋኝበት ውሃ መኖር ይገባ ነበር አለበለዚያ ክንፍ አይኖረውም ነበር። እዚያ... አንድ ዛፍ በምድር **ላይ** ማደግ ከመቻሉ በፊት፡ ዛፉ የሚያድግበት መሬት በመጀመሪያ መኖር ነበረበት፡ አለበለዚያ ዛፍ አይኖርም ነበር።

70 ስለዚህ፡ አያችሁ፡ በሰው ልብ ውስጥ አንዳች ነገርን የሚፈልግ ነገር እስካለ ድረስ፡ ለዚያ ጥሪ ምላሽ የሚሰጥ፡ ጥሪውን የሚያረካ አንዳች ነገር ውጭ መኖር አለበት።

71 አንዲት ሴት... ከጥቂት ጊዜ በፊት በሞተች አንዲት ሴት ላይ የአስከሬን ምርመራ ተደርጎ ነበር። እናም፡ እ—እነርሱ እንዳሉት፡ ለሞቷ ምክንያት የሆነው፡ ያለማቋረጥ፡ ሁልጊዜ ሸንኩርት ትበላ ስለነበር ነው። ሸንኩርት የማትበላ ከሆነ፡ ጭንቅላቷን ያክካት ነበር፡ እንዲሁም ሌሎች ነገሮች ይፈጠሩባት ነበር፥ ምክንያቱን ሊረዱት አልቻሉም ነበር። ስለዚህ የአስከሬን ምርመራውን ሲያደርጉ፡ በሴትየዋ ውስጥ የሆነ ዓይነት ሕዋሳት ዕጢ አገኙ፡ ለ—ለዕጢውም ስም አውጥተውለት ነበር። ያንን ዕጢ ወስደው ቀይ ሽንኩርት ባለበት ጎድጓዳ ሳህን ውስጥ ሲያኖሩት፡ በአንድ ሌሊት ውስጥ ቀይ ሽንኩርቱን አሟሟው። አያችሁ? ምን ነበር? በሴትየዋ ውስጥ ቀይ ሽንኩርት የሚፈልግ አንዳች ነገር ነበር፡ ቀይ ሽንኩርት ባይኖር ኖሮ ያ ዕጢ አይኖርም ነበር።

72 በሌላ አነጋገር፡ ፍጥረት ከመኖሩ በፊት፡ መጀመሪያ ፈጣሪ መኖር አለበት። አያችሁ?

73 አሁን፡ በሰው ልብ ውስጥ ጥልቅ ፍላጎት ካለ... ልክ እንደ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሬስባይቴሪያን፡ እስከ ካቶሊክ፡ እነዚህ ሁሉ ሌሎቹም፡ ያንን ብቸኛ እውነተኛ መንገድ ለማግኘት እንደሚሞክሩት፡ በካህናቶቻቸውና በፓስተሮቻቸው፡ እንዲሁም በመሳሰሉት፡ "እውነተኛው መንገድ ይህ ነው፡" ተብለው እንደሚነገሩት ነው። እነርሱም እንዲህ ይላሉ፡ ካህኑ፡ "ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውጭ መዳን የለም" ይላል።

74 እንግዲህ፡ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የራሱን... የራሱን ሃሳብ ይይዛል። አንዳንዶቹ አያምኑበትም፡ ነገር ግን በተግባራቸው ያሳዩታል። ተግባራችሁ ከቃላችሁ በላይ አጥብቆ ይናገራል። ይሄ ልክ... በሌላ አነጋገር፡ ከካቶሊክ በበለጠ ግብዞች ናቸው። ካቶሊኩ፡ "ይህ ብቸኛው ትክክለኛ ነገር እንደሆነ አምናለሁ" ብሎ በግልጽ ይናገራል፡ ነገር ግን እነርሱ ያንን አያደርጉም። ይደብቁታል፡ ነገር ግን ተግባራቸው ምን እያሰቡ እንደሆነ ያረጋግጣል። አያችሁ?

75 አሁን፡ እንግዲያውስ ያንን ለማግኘት በሰው ልብ ውስጥ ፍላጎት ስላለ፡ አንድ ሰፍራ መኖር አለበት። የእግዚአብሔር ቃል ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ መልስ አለው ብዬ አስባለሁ። ስለዚህ እግዚአብሔር መልሱ አለው፡ አሁንም በመጻሕፍት ውስጥ እንፈልገው። እግዚአብሔር በቅዱሳን መጻሕፍት አማካኝነት ያንን ብቸኛ ሰፍራ፡ ብቸኛውን መሠረት (እንዲሁ ከሆነ ደግሞ፡ ብቸኛውን የሐይማኖት ተቋምን)፡ እግዚአብሔር ሰውን የሚገናኝበት ብቸኛ መንገድ ካሳየን፡ ያንን አጥብቀን መያዝ አለብን ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት፡ እርሱ የሚለውን አግኝተናልና።

76 አሁን፡ **ዘዳግም** የሚለው ቃል፡ ቃሉ ራሱ "ሁለት ሕጎች" ማለት ነው፡ **ዘዳግም** የሚለው ቃል። እግዚአብሔርም ሁለት ሕጎች አሉት። ሁለቱ ሕጎች፥ አንደኛው ለቃሉ አለመታዘዝና፡ መሞት ነው፥ ሁለተኛው ደግሞ ለቃሉ መታዘዝና፡ በሕይወት መኖር ነው። እነዚህ ሁለቱ ሕጎች ናቸው፡ ዘዳግም ማለትም እነዚያ ሁለት ሕጎች ማለት ነው። ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ቀርበውልናል። ከእነርሱ አንደኛው ሞት ነው፡ ሌላኛው ደግሞ ሕይወት ነው፥ ሕይወት እና ሞት። እግዚአብሔር በሕይወት ብቻ ነው የሚሰራው፡ ሰይጣንም በሞት ብቻ። እነዚህም ለዓለም በአደባባይ፡ በሁሉም ዓይን ፊት በግልጽ ታይተዋል፡ ለእኛም ምንም ማመካኛ የለንም። ከእነርሱ አንደኛው መላውን የሰው ዘር ወደ ሞት የፈረደው፡ ሕግ በተሰጠበት ጊዜ በሲና ተራራ ላይ ታይቷል፥ ሌላኛው ደግሞ ቅጣቱ በኢየሱስ ክርስቶስ በተከፈለ ጊዜ፡ መላውን የሰው ዘር ወደ ሕይወት ያመጣው፡ በቀራንዮ ተራራ ላይ የተሰጠው ነው። የዘዳግም ሁለቱ ሕጎች፡ በእነዚህ ሁለት ታላላቅ ነገሮች ተፈጽመዋል።

77 በድጋሚ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ፡ ሁለት ኪዳኖችም ተሰጥተው ነበር። አንደኛው ኪዳን ለአዳም የተሰጠ ሲሆን፡ ይህ ልክ እንደ ሕግ፡ በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነበር፥ "ይህንን **ካል**ነካህ፡ በሕይወት ትኖራለህ፥ ነገር ግን ይህንን **ከ**ነካህ፡ ትሞታለህ።" ያ ሕግ ነበር። ከዚያም ለአብርሃም የተሰጠ ሌላ ሕግ ነበር፡ ይህም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ፡ በጸጋ የሆነ ነው፥ "አንተንና ከአንተ በኋላ ያለውን ዘርህን አድኛለሁ።" አሜን! ያ የቀራንዮ ምሳሌ ነው እንጂ፡ የ—የ—የአዳም ኪዳን ዓይነት አይደለም፡ የአብርሃም ኪዳን ነው።

78 ነገር ግን አሁን እርሱ ሰውን ለአምልኮ የሚያገኝበት አንድ ሰፍራ ብቻ እንዳለ ሲናገር እንሰማለን። እዚሁ ጽሑፋችን ላይ አንብበነዋል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፡ ወደ እርሱ፡ እንመለሰበታለን።

79 እንግዲያውስ እግዚአብሔር ሰውን የሚያገኝበት አንድ ሰፍራ ብቻ ካለ፡ እኛ በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል። አሁን ዛሬ ጧት ወጎቻችንን ወደ ጎን እንተወውና፡ እና... በዚህ የእሁድ-ትምህርታችን ላይ፡ ያንን አንድ ሰፍራ ማግኘታችንን በሚገባ እናረጋግጥ። ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር እዚህ ተናግሯል፡ በሌላ በማንኛውም ሰፍራ አይቀበላችሁም። በማንኛውም ሌላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ አይቀበላችሁም። በእርሱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ፡ እርሱ የሚቀበላችሁ ብቸኛ ሰፍራ እርሱ ነው።

80 አሁን፡ "ምን ትላለህ፡ ወንድም ብራንሃም? እኔ ቅን ከሆንኩስ?" በፍጹም።

81 አስታውሱ፡ ኢየሱስ በዘመኑ ከነበሩት ቅን ለነበሩ፡ አምላኪዎች ጋር ተነጋግሯል፡ እርሱም፡ “በከንቱ ያመልኩኛል” አላቸው። ከልባቸው ጥልቅ የሆነ እውነተኛና፡ ትክክለኛ አምልኮ ነበራቸው። “የሰውን ትእዛዝ፡ እንደ ትምህርት እያስተማራችሁ በከንቱ ታመልኩኛላችሁ፡” ወይም የሐይማኖት ተቋማዊ የሐይማኖት መግለጫቸውን። ቅን፡ አክብሮት ያላቸው፡ ሊሆኑ በሚችሉት መጠን ሃይማኖተኛ የሆኑ ነበሩ። ይህ ደግሞ በፈሪሳውያን ዘንድ ብቻ የተጀመረ አዲስ ነገር አልነበረም። እዚህ ምድር ላይ በተፈጥሯዊ ልደት የተወለዱት፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት አምላኪዎች፡ ቃየንና አቤል፡ በትክክል በተመሳሳይ አመለካከት ነበር የመጡት።

82 ቃየን ልክ እንደ አቤል ሃይማኖተኛ ነበር። ሁለቱም መሠዊያዎችን ሠርተዋል። ሁለቱም እግዚአብሔርን ይወዱ ነበር። ሁለቱም መሥዋዕት አቅርበዋል። ሁለቱም አምልከዋል። ሁለቱም አሥራት ከፍለዋል። ሁለቱም ሁሉንም ነገር በተመሳሳይ መልኩ አድርገዋል። ነገር ግን አቤል፡ **በእምነት** እርሱም “መገለጥ” በሆነው አደረገ፡ የእግዚአብሔር ቃል ተገለጠ፡ ግልጽ ሆነ፡ ታየ፡ ተረጋገጠ። ክብር ይሁን! ቃየን መሥዋዕትን አቀረበ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አላረጋገጠለትም። እግዚአብሔር አምልኮን ፈለገ፡ ቃየንም መሥዋዕቱን አቀረበ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አላረጋገጠለትም። ነገር ግን በእውነተኛው መሰመር...

83 እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ “እንግዲህ፡ የኔ ቤተ ክርስቲያን ናት። የኔ... ”

84 አንድ ደቂቃ ጠብቁ። እግዚአብሔር የራሱን ቃል እርሱ በተናገረበት በራሱ ቃላት ይተረጉመዋል። አያችሁ፡ ቃየን እንዲህ አለ፡ “እኔ ሃይማኖተኛ ነኝ። ፈጣሪዬን የምወድ ነኝ። ይህንን ያማረ መሠዊያ አቀርብልሃለሁ። ይህንን መሥዋዕት አቀርብልሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ ስለምወድህ፡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ አዘጋጅቻለሁ።” አቤልም ተመሳሳይ ነገር ነው ያለው። አሁን፡ የተረጋገጠው፡ የጻናው ነው። እግዚአብሔርም ወረደና የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ፡ ምክንያቱም በመገለጥ ተቀባይነት ያለውን የእግዚአብሔርን እውነተኛ መሰመር አግኝቶ ነበርና።

85 አሁን ያ የቃየን መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ አልፎ፡ ትክክል አሁን እስከዚህ መጨረሻው ዘመን ድረስ ሲመጣ ተመልከቱ። መሠረታዊ ነበርን? ልክ እንደ ሌላኛው እርሱም መሠረታዊ ነበር።

86 ነቢዩን በለዓምንና ነቢዩን ሙሴን ተመልከቱ። ሁለቱም ሰባት መሠዊያዎች፡ የይሖዋ የእግዚአብሔር መሠዊያዎች ነበሯቸው፡ በእያንዳንዳቸውም ላይ ደም ነበር፥ ያ ብቻም ሳይሆን፡ በእያንዳንዳቸው ላይ አውራ በጎች ነበሩ። በቁጥር ትንታኔም፡ ልክ ትክክለኛው ቁጥር፡ **ሰባት**፡ “ፍጹም” የሆነ፡ ሰባት አውራ በጎች። የሁለቱም መሠዊያዎች፡ ፈጽሞ ተመሳሳይ ነበሩ። አንደኛው መሠረታዊ እንደነበረው ሁሉ፡ ሌላኛውም እንዲሁ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር የማንን አረጋገጠ? አያችሁ? አያችሁ? በቃሉ ውስጥ የነበረውን ነው። መሠረታዊ መሆን ብዙም ትርጉም የለውም፥ ዋናው የእግዚአብሔር መገለጥ ነው።

87 አሁን አስቡ! እነዚህ ሰዎች፡ (እነዚህ ፈሪሳውያን) ለምን በኢየሱስ ተጠርተው በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ተቀመጡ፡ “በከንቱ ያመልኩኛል፡” ያለው ለምንድን ነው? ያመልኩታል፥ ትክክለኛ አምልኮ፡ ከልባቸው የሆነ እውነተኛ

አምልኮ ነበር። “እናንተ... በከንቱ ታመልኩኛላችሁ።” እንዴት? የሰውን ወግ የሆነ ትምህርት እያስተማራችሁ። “ስለዚህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በሕዝቡ ዘንድ ከንቱ ታደርጋላችሁ።”

88 የሜቶዲስትን መልእክት ባስተምራችሁ ኖሮ፡ በእናንተ ላይ ምንም ዓይነት ውጤት አይኖረውም ነበር፡ አሁን የሙሽራይቱ ጊዜ ነው። ሙሴ የኖህን መልእክት አስተምሮ ቢሆን ኖሮ፡ ምንም ውጤት አይኖረውም ነበር። ኢየሱስ የሙሴን መልእክት አስተምሮ ቢሆን ኖሮ፡ ምንም ውጤት አይኖረውም ነበር። ምክንያቱም አስቀድሞ የተወሰነው ዘር እዚያ አለ ያም ዘር ሊጠጣ የሚችለው ለዚያ ዘር በተሰጠው የውሃ ዓይነት ብቻ ስለሆነ ነው። አያችሁ? በሌላ በማንኛውም ሁኔታ አያድግም። የሚያሳድገው ትክክለኛው ሁኔታ መሆን አለበት።

89 አሁን፡ የዶሮ እንቁላልን ወስዳችሁ፡ በዶሮ ስር መሆን ሲገባው በማስፈልፈያ ማሽን ውስጥ ብታስገቡትም፡ ያለምንም ችግር ይፈለፈላል። በቡችላ ስር ብታስቀምጡትም ይፈለፈላል። እንዲፈለፈል የሚያደርገው ሙቀቱ፡ ሁኔታው ነው። ስለዚህ በትክክለኛው ሁኔታ ስር መሆን አለበት። ጥሩ በህይወት ያለ እንቁላል ወስዳችሁ በሞተች ዶሮ ስር ብታስቀምጡት ግን፡ አይፈለፈልም። አያችሁ? አያችሁ፡ ሁኔታው ነው ወሳኙ።

90 እንግዲህ፡ አሁን በምንኖርበት በዚህ ዘመንም ያለው ነገር እንደዚሁ ነው፡ ለዚህ ዘመን እግዚአብሔር የሚሰራበት መንገድ ምን እንደሆነ ማግኘት አለባችሁ። ማርቲን ሉተር ያገኘው ያንን ነው፡ ጆን ዌስሊ ያገኘው ያንን ነው፡ የጴንጤቆስጤ አማኞችም በዘመናቸው ያገኙት ያንን ነው። እግዚአብሔር የሚያደርግበት የራሱ ዘመንና ጊዜ አለው።

91 አሁን፡ የጴንጤቆስጤ አማኞችን እንመልከት። ያ ወንድም፡ አንዱ... እንደኛው... ዓይኑ የወጣ ይመስለኛል፡ በካሊፎርኒያ፡ በቀድሞው አዙዛ ጎዳና ላይ የጴንጤቆስጤን መልእክት በእውነት የጀመረው ጥቁር ወንድም ነበር። ጥቁር ስለነበር፡ ተሰቆበት ነበር። ተዘበተበት፡ ነገር ግን ለዚያ ዘመን የሚሆን መልእክት አመጣ። ትንሽ ሰውነት ያለው፡ ሰሙን እንኳ በቅጡ መፈረም የማይችል ሰው ነበር፡ ነገር ግን እነዚያ ስጦታዎች የሚመለሱበት ዘመን ይህ እንደሆነ ጌታ ገልጦለት ነበር፡ እነርሱም መጡ። **ምንም** ቢባልም፡ መጣ። ነገር ግን ሁሉም ሰው በዚያ ድባብ ውስጥ ገባ፡ ያም ዘመን እንደነበረ አየ፡ እነዚያም ሰዎች በልሳን መናገር እንደሚችሉና፡ የመሳሰሉትን ነገሮች እግዚአብሔር ሲያረጋግጥ አዩ፡ ሆነም። ነገር ግን በኋላ ሄዶ “ብቸኛው ማረጋገጫ ይህ ነው” ብሎ ሲያጠብቀው፡ ያም ገደለው። አያችሁ? ወደዚያው ሄደ፡ አያችሁ። ያ ነው ያበላሸው። ከዚያም **ይህንንና፡ ያንን** መለየትና፡ የሐይማኖት ተቋሞችን ማቋቋም ጀመሩ፥ አንደኛው በደመና ይመጣል፡ ሌላኛው ደግሞ በቁጥቋጦ ይመጣል ማለት ጀመሩ። ኦህ፡ ማይ፡ እንደዛ እየሆነ ሄደ።

92 የሐይማኖት ተቋሞች የሚያደርጉት ያንን ነው። አያችሁ? እግዚአብሔር የሐይማኖት ተቋም ጀማሪ አይደለም፡ ምክንያቱም የሐይማኖት ተቋም ባቢሎን ነው፡ እርሱ ደግሞ የሁከት አምላክ አይደለም። ሁሉንም... ያንን ለማየት ምሁር መሆን እንኳ አያስፈልጋችሁም። እሱ ባቢሎን ነው! አያችሁ? ወግ ነው (እስቲ

አሰቡት)፡ ቅን ሰዎች ናቸው። አሁን፡ አሁንም ቢሆን፡ ያንን ሰለሚያምኑ፡ እግዚአብሔር የሚገኝበት አንድ ትክክለኛ ሰፍራ አሁንም ያሰፈልጋል።

93 አሁን ቁጥር 2ን አሰተውሉ። "**እኔ** በመረጥኩት ሰፍራ አምልኩ።" መሥዋዕቱ፡ እርግጥ ነው፡ በመሥዋዕቱ ላይ ያመልኩበት የነበረው ነው። "**እኔ** የመረጥኩት ሰፍራ፥ እናንተ የመረጣችሁት፡ ሰው የመረጠው አይደለም። ነገር ግን **እኔ** በመረጥኩት፡ በዚህ ሰፍራ ታመልካላችሁ።" እንግዲያውሰ አንድ ሰፍራ ብቻ እንዳለ፡ ሌሎቹ ግን ከንቱ እንደሆኑ ያሳያል። **የእናንተ** ምርጫ መሆን የለበትም፡ ነገር ግን የእርሱ ምርጫ መሆን አለበት።

94 "ደህና፡ ወደ ቤተ ክርሰቲያን መሄድ አያሰፈልገኝም።" ወይም፡ "አንተ በጣም ጠባብ-አመለካከት ያለህ ነህ! ለምን፡ ሴቶች ሰለመሰበካቸው፡ እና... ወይም ሴቶች ጸጉራቸውን ሰለመቆረጣቸውና፡ ሰለ ወንዶች ሰለእነዚህ ሌሎች ነገሮች ትከራከራለህ። ለምን፡ አንተ በጣም ጠባብ-አሰተሳሰብ ያለህ ነህ!"

95 መልካም፡ በዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል አያሰፈልጋችሁም፡ ያንን ወደሚያደርጉበት ሰፍራ ሄዳችሁ መቀጠል ትችላላችሁ። አያችሁ? ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ እንዳለ ታገኙታላችሁ፡ ሰለዚህ፡ "በከንቱ ያመልኩኛል።" ኢየሱሰም ሰለዚሁ ተመሳሳይ ነገር ነው የተናገረው። አያችሁ?

96 በእያንዳንዱ ትንሽ ነጥብ፡ በሁሉም ነገር ውሰጥ፡ ታማኝ መሆን አለባችሁ። ሁልጊዜም ወይኑን የሚያበላሸው ት—ትንሹ ወይን፡ ት—ትንሹ ቀበሮ ነው። አንዳንዴ ትተዋላችሁ... ዋናው ነገር የምታደርጉት ታላላቅ ነገር ሳይሆን፡ ሳታደርጉ የምትተዉት ትናንሽ ነገር ነው። አሰታውሱ፡ የአንድ ሰንሰለት ጥንካሬ የሚለካው በደካማው መገጣጠሚያው ነው። "ወደ ውሰጥ ለመግባት መብት እንዲኖራቸው፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት **ሁሉ** የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው።" እግዚአብሔር ያለውን **ሁሉ** አድርጉ።

97 ቃሉ ሴቶች ረጅም ጸጉር እንዲኖራቸው ከተናገረ፡ እናንተ... በቅርቡ አንድ ሰው እንዲህ ብሎኝ ነበር፡ "እኔ በአለባበሰ ላይ ያተኮረ ሃይማኖትን አልሰብክም፡" አለኝ።

98 እኔም፡ "እንግዲያውሰ ወንጌልን እየሰበክህ አይደለም" አልኩት። አዎን።

99 እግዚአብሔር እዚያ በግልጽ አሰቀምጦታል፡ ምን ማድረግ እንዳለብን ተናግሯል። ወይ ታደርጉታላችሁ... ያ ተፈጥሯዊ፡ የሚጠበቅባችሁ ግዴታችሁ ነው። ምን ያህል ትንሽ ነገር... ምን... ቀላል ነገር። ኢየሱሰ፡ "ሁሉንም ትናንሽ ነገሮች የሚቀበሉ፡ ትናንሽ ነገሮችን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው" ብሏል። አንዲት ሴት ጸጉሯን እንድታሳድግ ማድረግ፡ ያ እንዲሁ... እንግዲህ ይህ፡ **እሷ** ልታደርገው የምትችለው ነገር ነው፡ ነገር ግን ያንን እንኳ አታደርግም። ያንን እንኳ አታደርግም።

100 "ኦህ፡ ታላላቅ ነገሮችን አሰተምረን" ይላሉ።

101 ቀላልና የተለመደውን ነገር እንኳ ማድረግ ሳትፈልጉ፡ ታላላቆቹን ነገሮች፡ እንዴት ልታሰተምሩ ትችላላችሁ? ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ የልባችሁ ሃሳብና ዓላማችሁ የተሳሳተ ነው።

102 ለእግዚአብሔር ያላችሁ ፍቅር ነው፡ “ጌታ ሆይ፡ ምንም እንዳደርግ ብትፈልግ ግድ የለኝም፡ ያንን ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ” የሚያሰኘው። ያኔ የሆነ ደረጃ ላይ እየደረሳችሁ ነው፡ ነገር ግን በዚያ መንገድ የማታደርጉት ከሆነ፡ እርሱ አድርጉት ባለው መንገድ...

103 የእርሱ ምርጫ ነው፡ “እኔ የመረጥኩት ስፍራ።” ከመሥዋዕታችሁ ጋር የምታመልኩት እዚያ ነው።

104 እናንተ... ቃየን መሥዋዕቱን አቀረበ፡ አቤልም የራሱን አቀረበ፡ ነገር ግን ወሳኙ ወደየትኛው ስፍራ እንደምትወስዱት ነው። እርሱ ወደመረጠው ስፍራ ከወሰዳችሁት፡ ትክክል ይሆናል፡ ይቀበለዋል፥ በዚያ ካልሆነ ግን፡ አይቀበለውም። ምንም አያገባውም፡ ያው ተመሳሳይ መሥዋዕት ቢሆንም፡ ምንም ይሁን ምን፡ ወደዚያ ወደ አንድ የተወሰነ ስፍራ ካልመጣ በቀር፡ አሁንም-... ተቀባይነት የሌለው ነው።

105 አሁን ይህንን መሥዋዕት የት ማቅረብ እንዳለብን ማወቅ እንፈልጋለን። ማወቅም እንችላለን... ሁላችንም ወደ ሰማይ መሄድ እንፈልጋለን። አይደል እንዴ? ደግሞም ሁላችንም ስህተት እንደሰራን እናውቃለን። ሁላችንም ኢየሱስ መሥዋዕቱ እንደሆነ እናምናለን። አሁን እርሱን ይዘን የት መሄድ እንዳለብን ማወቅ እንፈልጋለን፡ ያ—ያኔ ተቀባይነት ይኖረዋል። አያችሁ? በትክክል። መጽሐፍ ቅዱስ የት መውሰድ እንዳለብን ይነግረናል፡ አያችሁ፡ ተቀባይነትም ይኖረዋል፥ ከዚያ ውጭ ግን፡ ፈጽሞ ተቀባይነት አይኖረውም።

106 እስቲ እዚህጋር መሥዋዕቱ እንዲቀርብበት እርሱ የመረጠውን ቦታ፡ መሥዋዕቱን ሊያኖርበት የመረጠውን ስፍራ እናስተውል። ከእነዚህ ደጆች በማንኛውም ላይ ልታስቀምጡት አትችሉም፡ ነገር ግን እርሱ ሊያስቀምጠው በመረጠው ስፍራ ላይ፡ ስሙንም ደግሞ በዚያው ስፍራ አኑሯል። እዚህ ላይ የተናገረው ያንን ነው። ስሙን በዚያ ሊያኖር መርጧል። አሁን መጻሕፍትን ስለዚህ ስፍራ እንመርምር፡ ስሙን ያኖረበት ስፍራ ያ ነውና።

107 አሁን ከጽሑፉ እናንብብ። እዚህ ያስቀመጥኩት ትንሽ ማስታወሻም ነበረኝ እሱም... ዛሬ ጧት፡ መጣልኝ። የዚህን ምዕራፍ 2ኛ ቁጥር እንመልከት። አሁን፡ እዚህ በመስመር ላይ ስላሉት፡ ሰዎች ስል፡ ብዙ ማቆየት አልፈልግም። አሁን የዚህ 16ኛ ምዕራፍ ቁጥር 2፥

**አምላክህ እግዚአብሔር፡ በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ በመረጠው ስፍራ፡ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ከበግና ከላም መንጋ ፋሲካ ሠዋ።**

108 አሁን፡ ይህንን... ቅንነታችሁንና ልትናዘዙት የምትፈልጉትን ሁሉ፡ ወደ ሜቶዲስት መሠዊያ፡ ወደ ባፕቲስት መሠዊያ፡ ወደ ጴንጤቆስጤ መሠዊያ እንዲሁ ይዛችሁት ልትሄዱ አትችሉም፡ ነገር ግን የሆነ ቦታ ላይ... ስሙን ሊያኖርበት የመረጠውና፡ በዚያ ስፍራ ሊያገኛችሁ የመረጠው መሠዊያ አለ። አሁን፡ ሁሉንም ነገር በትክክል እንዲሰራ ካደረጋችሁ፡ ይሰራል፥ ሁሉም ነገር በሥርዓት ከተቀመጠ። በዚያ ሽቦ ላይ መቆራረጥ ካለ፡ ያ መብራት አይበራም፥ ምክንያቱም መሬት ላይ ወርዷልና። እናንተም ከእግዚአብሔር ቃላት አንዱን ወይም ከስፍራዎቹ አንዱን ወሰዳችሁ፡ በገዛ ልባችሁ ራስ ወዳድነት ያለበት ዓላማ ከኖራችሁ፡ የእግዚአብሔርን ኃይል እዚያው ላይ

ያቋርጠዋል። ያንን የምታደርጉት ብልጥ መሆን ስለፈለጋችሁ፡ ወይም ከሌላ ሰው የተለያችሁ መሆን ስለፈለጋችሁ፡ ወይም ሌላ ነገር ከሆነ፡ እዚያው ላይ ያቋርጠዋል፡ ፊውዙን ያቃጥለዋል። ተሳስታችኋል። በቅንነት፡ በሙሉ ልባችሁ፡ ተነሳሽነታችሁንና ዓላማችሁን ቀጥታ በእግዚአብሔር ላይ አድርጋችሁ መምጣት አለባችሁ። ከዚያም **የእርሱን** ስፍራ ፈልጉ፡ እርሱ የተናገረውን ስፍራ አግኙና፡ ወደዚያ አምጡት። እያችሁ?

109 ማርታንና ማርያምን ተመልከቱ። ኢየሱስ ይህንን ወንጌል (እርሱ መሲሕ እንደሆነ፡ የዘመኑን ብርሃን) ካስተማራቸው በኋላ፡ በተመለሰ ጊዜ፡ የተጠላና፡ የተገፋ ነበር። ኦህ፡ ፈሪሳውያንና ቤተ ክርስቲያናት ንቀውት ነበር። ነገር ግን ለእርሱ የልብ ወዳጁ የነበረው ወንድም፡ አልዓዛር ሞቶ ነበር። እርሱም በዚያው እንዳለ እንዲሞት ተወው፥ ወደ እርሱም ልከው ነበር፡ እርሱ ግን አልመጣም ነበር።

110 ነገር ግን ማርታን፡ ያላትን አመለካከት ተመልከቱ። "ጌታ ሆይ፡ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፡" አለችው። ትክክለኛውን ማዕረግ ሰጠችው፥ ጌታ፡ በትልቁ ፊደል L-o-r-d፡ **ያህዌ**፡ ይሖዋ። ክብር ይሁን! "አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፡ ወንድሜ ባልሞተ ነበር።" ሕይወትና ሞት በአንድ መስመር፡ ወይም በአንድ ቤት ውስጥ ሊጣመሩ አይችሉም። "አንተ... እርሱ ባልሞተ ነበር።"

111 ኢየሱስም እንዲህ አላት፡ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፡" ይላል እግዚአብሔር። እያችሁ? አስቀድሞ፡ "ወንድምሽ ዳግመኛ ሕያው ይሆናል" ሲላት።

112 እርሷም፡ "አዎ፡ ጌታ ሆይ፡ ያንን በእውነት አምናለሁ። እንደ አንዲት አይሁዳዊት፡ የሙታን አጠቃላይ ትንሣኤ እንደሚኖር አምናለሁ፥ እንዲሁም ወንድሜ በአምልኮው ያን ያህል ታማኝና ቅን እንደነበረ አምናለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረለት፡ ያ መሲሕ አንተ እንደሆንክ አምናለሁ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃሉን በአንተ በኩል ማረጋገጡ የዚህ ዘመን መልእክተኛ አንተ መሆንህን ያሳያልና። አንተ ያ መሲሕ ነህ። ሥራዎችህ እግዚአብሔር አንተን ያ መሲሕ እንድትሆን ወደዚህ እንደላከህ ስለሚመሰክሩ፡ ሊመጣ የነበረው ያ ክርስቶስ አንተ እንደሆንክ አምናለሁ" አለችው። ኦህ፡ ማይ! አሁን የሞተሩ ጥርሶች ወደየቦታቸው መግባት ሲጀምሩ ተመልከቱ። እያችሁ?

113 አሁን፡ እንዲህ የማለት መብት ነበራት፡ "ወንድሜን ለማስነሳት ለምን አልመጣህም? ለምን አልፈወስከውም? ሌሎችን ፈውሰሃል። የቅርብ ጓደኛህ ነበር፡ አሁን ግን ምን እንደተፈጠረ ተመልከት" የማለት መብት ነበራት። አይ፡ በጭራሽ፡ እንደዚህ ዓይነቱ ዓላማ የትም አያደርስም።

114 "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው አንተ ልክ ያው እንደሆንክ አምናለሁ። መሲሑ የሚመጣበት ዘመን ይህ እንደሆነ አምናለሁ፥ ይህንን ስንጠብቅ ነበር። ሌሎቹ የሚሉት ምንም አያገባኝም። ባየሁትና በቃሉ በሰማሁት መሠረት፡ ቃሉ በአንተ እንደተረጋገጠ፡ አንተ ያ መሲሕ እንደሆንክ፡ በሙሉ ልቤ አምናለሁ።" እያችሁ፡ በውስጧ ጥልቅ የሆነ፡ የ—የምትጠይቀው አንዳች ነገር ነበራት፡ ነገር ግን በትክክለኛው መስመር መምጣት ነበረባት።

115 ሮጣ ወደዚያ በመሄድ እንዲህ ብትል ኖሮስ፡ "አንተ ያ መሲሕ ነኝ እንደሆንክ ነግረኸኛል! ታዲያ የለመንህን ለመመለስ እንኳ፡ የጨዋነት ያህል አክብሮት

አላሳየህም፥ እኛ መገብንህ በቤታችንም አኖርንህ፡ ሁሉንም ነገር አደረግንልህ፡ ቆምንልህ፡ ደግሞም ከነዚያ የሐይማኖት ተቋማት እንድንወጣ ባዘዝከን መሠረት፡ ቤተ ክርስቲያኖቻችንን ትተን ወጣን።" እያችሁ? "ይኸው ጥለነው ወጥተናል፡ አሁንም እንደተገለልንና እንደከዳተኞች ተቆጥረናል። ይህን ሁሉ ነገር ላንተ አድርገን፡ ጥሪዬን ለመመለስ እንኳ ተራ ጨዋነት አይታይብህም? " አሁን፡ በእርግጥም፡ ያ መብት ነበራት።

116 ስለ አጭር ጸጉርሽ እንደምትይው ማለት ነው፡ "እኔ አሜሪካዊ ዜጋ ነኝ። ቁምጣ መልበስ እችላለሁ፡ የፈለግሁትን ማድረግ እችላለሁ፡ ሕገ ወጥ አይደለም።" ያ መብትሽ ነው፡ ነገር ግን በግ ሁልጊዜም መብቱን አሳልፎ ይሰጣል። ኧ-ህ። በግ ከሆንክ! ከጸጉሩ በስተቀር ምንም የለውም፡ ያንን አሳልፎ ይሰጣል። ያ እግዚአብሔር-የሰጠው መብቱ ነው፡ ነገር ግን አሳልፎ ይሰጠዋል።

117 "የፈለግሁትን የሐይማኖት ተቋም የመቀላቀል መብት አለኝ።" ያ ፍጹም ልክ ነው፡ ነገር ግን ያንን መብትህን አሳልፈህ ትሰጣለህ። እያችሁ?

118 እዚያው በፊቷ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ ስትል፡ መብት የነበራትን ነገር ሁሉ አሳልፋ ሰጠች።

119 እርሱም እንዲህ አላት፡ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ። በእኔ የሚያምን፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ይሆናል። ሕያው የሆነና በእኔ የሚያምን ሁሉ ለዘላለም አይሞትም። ይህንን ታምኛለሽን? " እያችሁ፡ ገና በትክክል መስመር ላይ ያልገባችበት ሌላ አንድ ትንሽ የሞተር ጥርስ ነበር። እያችሁ?

120 "አዎን፡ ጌታ ሆይ! አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ፡ ክርስቶስ እንደሆንክ አምናለሁ!" ኦ ወንድሜ፡ ያኔ ሁሉም ነገር ለመቀጣጠል ዝግጁ ነበር። እያችሁ?

121 "የት አኖራችሁት? " እያችሁ? ምን እንደተፈጠረ ታውቃላችሁ።

122 እያችሁ፡ መሥዋዕታችሁን ከመቀበሉ በፊት ወደዚያ ትክክለኛ ሰፍራ መግባት አለባችሁ። እያችሁ፡ ወደዚያ መድረስ አለባችሁ። አሁን፡ ተመልከቱ።

**... እግዚአብሔር ስሙን ሊያኖርበት በሚመርጠው ሰፍራ።**

**እርሾ ያለበትን እንጀራ በእርሱ አትብላ፥...**

123 በመሥዋዕቱ ውስጥ ያ የምን ምሳሌ ነው? ከማንኛውም የሐይማኖት መግለጫ ጋር አትቀላቅሉት፡ ቃሉ ብቻ መሆን አለበት። "**እርሾ ያለበት እንጀራ አይሁን**።" እርሾ ማለት... በማንኛውም ነገር ውስጥ እርሾ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። "ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካዋል፡" ሊጡ ሁሉ አካሉ ነው። በክርስቶስ ውስጥ አንዲት ቅንጣት የሐይማኖት ተቋም ወይም የሐይማኖት መግለጫ መጨመር አትችሉም። በፍጹም፡ አይሆንም፡ ያ አይሰራም።

124 ያለፈውን ሐሙስ ማታ መልእክት ታስታውሳላችሁ? አሮጌው ባላችሁ መሞት አለበት። በትክክል። አዲሱ ባላችሁ ቃሉ ነው።

**... ሰባት ቀን እርሾ የሌለበትን እንጀራ** ብላበት፡...

125 "**ሰባት ቀን**፡" ያ የምኑ ምሳሌ ነው? ሙሉዎቹ የሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት፡ ሰባት ዘመናት። ለምን ለሰባት ቀናት መብላት አስፈለጋቸው? ከምን በፊት? ከመውጣታቸው በፊት። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ፡ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው፡ መኖር ያለበት ለዚያ ዘመን በተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል

ላይ ብቻ ነው። ስለዚህ የሮማውያን፣ የሜቶዲስት፣ የባፕቲስትና፣ የጴንጤቆስጤ የሐይማኖት መግለጫዎች ሁሉ የሞቱ ናቸው።

126 አሁን ተመልከቱ።

… በዚያም፣ **የመከራን እንጀራ እንኳ፥…**

ስለእርሱ ተሰደዱ፥ ሉተር፣ ዌስሊ፣ ጴንጤቆስጤዎች፥ ሁሉም ተሰደዱ፣ እናንተም እንዲሁ ትሰደዳላችሁ።

**… ከግብፅ ምድር በችኮላ ወጥተሃልና፥… በሕይወትህ ዘመን ሁሉ… ከግብፅ ምድር የወጣህበትን ቀን ታስብ ዘንድ።**

**በዳርቻህም ሁሉ ሰባት ቀን እርሾ ያለበት እንጀራ ከአንተ ዘንድ… አይታይም፥…**

127 በውኗ የክርስቶስ ሙሽራ ውስጥ፣ በጨለማው ዘመን በሮም መንግሥት ምክንያት ከሞተች በኋላ፣ "የስንዴ ቅንጣት በምድር ላይ ወድቃ ካልሞተች በቀር፣" መሞት ነበረባት። ሙሽራው መምጣት ነበረበት፣ የእግዚአብሔር ፍጹም የሆነው እውራ ሥራ። ሁላችሁም ስለዚህ ያስተላለፍኩትን መልእክት ሰምታችኋል።

128 አንድ ቀን እዚያ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ፎረስት ሎን፣ ቆሜ ሳለሁ፣ ልቤ ዘለለ። ስንቶቻችሁ ፎረስት ሎን ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? እዚያ አንድ… የሙሴ ሐውልት በ—በ… -አንጀሎ፣ ማይክልአንጀሎ፣ ይመስለኛል የተሰራው። ቀኝ ጉልበቱ ላይ ካለው፣ ግማሽ ኢንች ጥልቀት ያለው ሰብራት በቀር፥ ፍጹም ሐውልት ነው። አስጎብኚውም… እየተመለከትኩ ሳለ፣ አመላከተኝ። እርሱም እንዲህ አለ፣ "ማይክልአንጀሎ የ—የሕይወት ዘመኑን ለመሥራት ሲሞክር አሳልፏል… እርሱ ቀራፂ ነበር፣ የሙሴንም መልክ ለመሥራት ይጥር ነበር። በአእምሮው ውስጥ፣ ሙሴ ምን ሊመስል እንደሚገባው ያሰብ ነበር። ያንን በልቡ ውስጥ ይዞ ነበር፣ ሙሴ ምን ሊመስል እንደሚገባው። የሕይወት ዘመኑንም አሳለፈ፥ እዚህ ጋር ጥቂት ይቀርፀዋል፣ ይፈቀፍቀዋል፣ ወደ ኋላ ቆሞም ይመለከተዋል። ከዓመት ዓመት፣ በእርሱ ላይ ሠራ። በመጨረሻም ሲጠናቀቅ፣ ወደ ኋላ ተመልሶ ጨርቁንና መዶሻውን ካስቀመጠ በኋላ፣ ሐውልቱን ተመለከተ። በልቡ የነበረው የሙሴ ምስል በጣም ፍጹም ከመሆኑ የተነሳ፣ ራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድረስ፣ መዶሻውን ይዞ መታው፣ 'ተናገር' ብሎም ጮኸ!" ይህ የ**ማይክልአንጀሎ እውራ ሥራ** ተብሎ ተጠራ። በዚያ ቀራፂ ውስጥ የነበረው ያ ታላቅ ነገር፣ ሙሴ ምን መሆን እንዳለበት የነበረው ያ ራዕይ፣ የታላቁን አባት የእግዚአብሔርን አምሳያ በምሳሌ የሚያሳይ ብቻ ነበር።

129 እርሱ አባት ስለሆነ፣ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፣ በልቡ ውስጥ፣ ልጅ ነበረው። ዳሩ ግን ያ ገና በቃሉ ዘሮች ውስጥ ነበር። ሰውንም ፈጠረ፣ ነፃ የሞራል ምርጫም ሊሰጠው ግድ ነበር፣ ሆኖም ያ ሰው ወደቀ። ነገር ግን ከምድር አፈር ሰውን የሠራው፣ ታላቁ ቀራፂ እግዚአብሔር፣ በዚያ አልረካም፣ ሰውን እንደገና መሥራት ጀመረ። ኖኅንም ሠራ፣ እርሱም ሰክሮ ሞተ። ቃሉን ለመጠበቅ ያልቻለውን ሙሴን ሠራ። በመከራ ጊዜ የሚሸሹ ነቢያትን ሠራ። እርሱን የሚያንፀባርቅ ባህሪውን በልቡ ውስጥ የነበረውን ልጅ ምን መሆን እንዳለበት የ—የሚያሳይ፣ አንድ የጥበብ ሥራ፣ እስኪፈልግ ድረስ፣ መገንባቱንና መቅረፁን ቀጠለ።

130 አንድ ቀን፡ እዚያ ዮርዳኖስ ላይ፡ ያ አውራ ሥራ ከተሰራና ከተጠናቀቀ በኋላ፡ እነሆ በርግብ ክንፍ ላይ... ወርዶ መጣ፡ እንዲህም አለ፡ “ይህ እርሱ ነው!” በዚህ አውራ ሥራ በጣም ተደስቶ ስለነበር ፍጹማን ላልሆንነው፡ ለቀሪዎቻችን እንዲሞት በቀራንዮ ላይ መታው፥ ይህም ደሙን በማፍሰስ፡ ብዙ አውራ ሥራዎችን (ሙሽራይቱን) ወደ ልጁ እንዲያመጣ ነው። አውራ ሥራው ጠባሳ አለበት ምክንያቱም እንዲህ ያለውን የአውራ ሥራ ለማየት በነበረው የእግዚአብሔር መነሳሳት፡ ለሁላችን እርሱን መትቶታልና። አያችሁ? ፍጹማን ያልሆንነውን እኛን ፍጹም ለማድረግ፡ እዚያ ሞተ። አውራ ሥራው።

131 አስተውሉ፡ በዚህ ስፍራ እንዲህ አለ፥

**... ሰባት ቀን ይህን እርሾ የሌለበትን እንጀራ ትበላላችሁ...**

132 አሁን፡ እንጀራ በምሳሌነት ተቀምጧል። ኢየሱስ፡ “ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡ ነገር ግን በቃል ሁሉ እንጂ” አለ። የ—የሐይማኖት ተቋማት እንድታምኑት እንደሚያደርጉት ከዚህም ከዚያም የተወሰደ ቃል ብቻ ማለት አይደለም። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ነው! እርሱ ራሱ እግዚአብሔር በፊደል መልክ ሲሆን፡ “ዘር” ተብሎ ይጠራል። በዚያም ቃል ላይ ትክክለኛና ያልተበረዘ እምነት ያንን ዘር ወደ ሕይወቱ ያመጣዋል።

133 ማታ በመለየት አገልግሎቶች፡ በሌሎችም ነገሮች ሁሉ የምታዩት ልክ ይኸው ነው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የገባው ተስፋ ነውና። በአጠገቤም ቆሞ ያንን ነገረኝ፡ እነዚህ “አስመሳዮች ይነሳሉ፡ ዳሩ ግን ጸንተህ ቁም” ብሎ ነገረኝ። አምነዋለሁ። ማንንም ለመጉዳት፡ የራስ ወዳድነት ተነሳሽነት ኖሮኝ ሳይሆን፡ ነገር ግን ለእግዚአብሔር እንድገዛና የጠራኝን ሥራ እንድሠራ ስለሆነ፡ እነዚህን ነገሮች እናገራለሁ። እግዚአብሔርም መልሶ ያረጋግጠዋል፡ እውነት መሆኑን በማጽናት፡ ስጦታውንም መሰዋዕቱንም ይቀበላል። በዚህ ላይ ምንም ጥያቄ የለውም! አሁን ያንን ቃል ተመልከቱ!

134 አሁን፡ እዚህ ጋር፡ “**ሰባት ቀን፡**” ማለት ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን እንደሆነ እናስተውላለን። አሁን፡ ያ የአውራ ሥራ መሞት እንደነበረበት፡ ሁላችንንም ለመዋጀት ከሙታን ይነሳ ዘንድ፡ ከዚያም በጴንጤቆስጤ የተስተካከለች ቤተ ክርስቲያን ነበረችው፡ ዳሩ ግን ያች ቤተ ክርስቲያን በመሰዋዕትነት ማለፍ ነበረባት፥ የሮማውያን ዓለምም ገደላት፡ በመሬት ውስጥም ቀበራት።

135 አሁን ሰሙ ሊመጣልኝ ያልቻለ፡ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ፡ በጣም እንዳሾፈብኝ፡ “ከአጋንንት ሁሉ፡ ዊሊያም ብራንሃም ነው፡” እንዳለ ነው። አያችሁ፡ ዲያብሎስ ለማለት የሚሞክረው ያንን ነው። እርሱም እንዲህ አለ፡ “ራእዮችም ሆኑ ነገሮች፡” እንዲህ አለ፡ “እነዚህ የአጋንንት ናቸው” አለ፡ እንዲህ አለ፡ “ወይም፡ እርሱ የሆነ ዓይነት አስማተኛ ነው፡ ወይም ከተፈጥሮ በላይ በሆነ የስሜት ሕዋስ ግንዛቤ ይሠራል” አለ። ምሁራዊው ዓለም ሁልጊዜ ይህን ለማብራራት ይሞክራል።

136 ኢየሱስንም ሊረዱት የሞከሩት እዚያ ጋ ነው። “እነዚህን ነገሮች እንዴት ታደርጋለህ? ያደረገውስ ምንድን ነው? ”

137 እርሱም እንዲህ አለ፡ “አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ። የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት... ከእግዚአብሔር ነበረ ወይስ ከሰው? ” አያችሁ?

138 እነርሱም፡ “ልንነግርህ አንችልም” አሉ።

139 እርሱም፡ “እኔም አልነግራችሁም” አለ። ልክ ነው። ቀጠሉም። “ከዚያም ወዲህ ማንም አንዳች አልጠየቀውም።” አያችሁ? አቋረጣቸው እንጂ፡ ስለዚያ ምንም አልነገራቸውም፥ አያገባቸውምና። የሚሠራው ሥራ ነበረው ፈጸመውም።

140 እግዚአብሔር እኛንም ያንኑ እንድናደርግ ይርዳን። የዲያብሎስን ጥያቄዎች መመለስ አያስፈልገንም፡ ልክ ነው፡ “አንተ ከሆንክ፡ **ይህንን-እና-ያንን** አድርግ።” ለዚያ ወንጌል ኃላፊነት አለባችሁ፡ ሰባኪው ኃላፊነት አለበት፡ ያ ነው በቃ፥ እንዴት እንደተጻፈ ሳይሆን፡ እርሱን ለመናገር ብቻ ኃላፊነት አለበት።

141 እንደ አገልጋይ፡ ነቢይ ከሆንክ፡ ለእግዚአብሔር ኃላፊነት አለብህ። የሚመጡትም ራእዮች ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያበሩትና ምንነቱንም የሚያሳዩ ከሆነ፡ በዚያ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላለው እያንዳንዱ ቃል ኃላፊነት አለብህ፡ ምክንያቱም ሁሉም የተጻፈው ልክ እንደአንተ ባሉ ሰዎች ነውና። “የጥንቱ እግዚአብሔር፡ በነቢያት ተንቀሳቅሶ፡ ቅዱ-... ቅዱሱን መጽሐፍ ጻፈ።” አያችሁ? ማንኛውም እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይም አንዲቱን ቃሉን ሊክድ አይችልም፡ ነገር ግን እያንዳንዱን ቃል አምኖ ያንኑ ይሰብካል። ከዚያም እግዚአብሔር በዚያ መስመር ውስጥ ሆኖ ቃሉ በተሰፋው መሠረት ልክ እንደተነገረው እንዲፈጸም የማድረግ ግዴታ አለበት፡ ዘሩም ያድጋል።

142 አሁን፡ በድጋሚ በፍጥነት፡ አስተውሉ፡ ይህ እንጀራ ሊበላበት የነበሩት ሰባቱም ቀናት፡ በሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ሁሉ ውስጥ መሆኑን እዚህ እናገኛለን። አሁን፡ መሞትና ወደ መሬት ውስጥ መግባት ሲኖርበት ነው።

143 ስለእኔ የተናገረውም ይህ ነቃፊ፡ እንዲህ አለ፡ “እናንተ ሰዎች የምታመልኩት አምላክ፡ በጨለማው ዘመን ተቀምጦ፡ ነፍሰ ጡር የሆኑትን እናቶች፡ አንዳንዶቹም ትንንሽ ሕፃናትን አቅፈው፡ ቅን የሆኑ ሰዎች፡ ወደ አደባባይ ሲጣሉ አንበሶችም ቆራርጠው ሲጥሏቸው፡ እነርሱም ሲጮኹ ይመለከት የነበረው አምላክ፥ በመስቀል ላይ ሰቅለው ሲያቃጥሏቸው፥ ሴቶችን ራቁታቸውን ሲያስቀሩ፡ ወጣት ደናግልንም፡ **እንደዚህ** ወደ ኋላ ገፍትረዋቸው፡ አንበሶችንም ሲለቁባቸው ይመለከት የነበረው አምላክ ነው።” እርሱም ሲናገር፡ “በሰማይ ላይ ተቀምጦ፡ ዙፋኑ ላይ ሆኖ፡ ወደ ታች እየተመለከተ በዚህ ደስ ይለኛል የሚል አምላክ ነው፡” አለ።

144 እንግዲህ፡ አያችሁ፡ ይህ ከዲያብሎስ የሆነ ምሁራዊ አስተሳሰብ ነው። ያ ሰው መንፈሳዊ ቢሆን ኖሮ፡ ያች የሰንዴ ቅንጣት መሞት እንዳለባት፥ በሮማውያን ካቴድራል ውስጥ መቀበር እንዳለባት በተረዳ ነበር።

145 ነገር ግን የመጀመሪያዋ ትንሿ የሕይወት ቡቃያ በማርቲን ሉተር የተሃድሶ እንቅስቃሴ ውስጥ ወጣች፡ ይኸውም፡ “ጻድቅ ካህን በሚያደርገው በተባረከ ሥርዓት አይኖርም፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል እንጂ። ‘ጻድቅ በእምነት ይኖራል!’” እርሱም ሁለት ቡቃያዎችን አወጣ። የሰንዴዋም ቅንጣት ማደግ ጀመረች።

146 ከዚያም ጆን ዌስሊ መጣ በዚያም ላይ ጨመረበት። (ሌሎችም ብዙዎች ነበሩ፡ እነዚያ... ዝዊንግሊም እነርሱም መጡ የድንግልንም ውልደት ካዱ፡

እርሱም በዚያው ከሽፈ።) ዳሩ ግን ሜቶዲስት መጣ፡ ዛላው፡ ጽጌው፡ የሚሰዮናውያን ዘመን። እነርሱም ቅድሰናን ሰበኩ፥ ዛላውንም ጨመሩ።

147 ከዚያም ጴንጤቆስጤዎች በገለባው መጡ፡ የተመረጡትንም ሊያሳስቱ፡ እስኪቃረቡ ድረስ። ልክ እንደ እውነተኛ የሰንዴ ቅንጣት ይመስላል፡ ሲከፈት፡ ምንም ሰንዴ የለበትም። ዳሩ ግን ሕይወት በገለባው ውስጥ እያለፈ ነበር።

148 አሁን፡ ከታላቅ ሰብሰባ በኋላ በ—በየሦስት ዓመቱ፡ ምን እንደሚፈጠር፡ አስተውላችኋል? የሐይማኖት ተቋም። ይህ ሃያ ዓመታት ሆኖት ምንም የሐይማኖት ተቋም የለም። የሞትከው የተወደድክ በግ ሆይ፡ ከቶ ይህ አይሁን። በዚህ ትውልድ ባልፍ፡ ይህን መልእክት የሚያምኑ ሰዎች ለሐይማኖት ተቋም ከቶ እጅ አይሰጡ! እግዚአብሔር... ባላችሁበት ቦታ ትሞታላችሁ! ያንን አስታውሱ! በመካከላችሁ የሐይማኖት ተቋምን በምታነሱበት በዚያችው ሰዓት፡ ምንም ያህል ቅን ብትሆኑ ግድ የለኝም፡ ይህንን ቃል እንዲያጸና ከመንፈስ ቅዱስ ይልቅ ሰውን መሪ አድርጋችሁ ስትወስዱ፡ ያቺ የምትሞቱባት ሰዓት ናት! እውነተኛው ዘር እንዲህ ሊያደርግ አይችልም፡ ምክንያቱም ከዘሩ በኋላ የሚቀር ምንም ነገር ሰለሌለ፡ መጀመሪያ ላይ የነበረው ያው አንድ ዓይነት ነገር ነው። ዳግመኛ የሰንዴ ቅንጣት ታፈራ ዘንድ በመሬት ውስጥ የወደቀችው ሙሽራይቱ ናት።

149 አስተውሉ፥

**... ሰባት ቀን እርሾ የሌለበትን እንጀራ ትበላላችሁ...**

150 ከሙሽራይቱም ጋር ይሆናል...

151 አሁን፡ ያቺ የቀድሞዋ እየጮኸች የምትጸልይ ሜቶዲስት እናት፡ እንዲሁም ሌላም የነበረቻችሁ ሰዎች፡ "በልሳን ካልተናገረች፡ አትገባም" ብላችሁ ታስቡ የነበራችሁ። ያ ውሸት ነው! እርሷ ዛሬ እናንተ ያላችሁ ያው አንድ ዓይነት መንፈስ ቅዱስ ነበራት፡ ዳሩ ግን በዛላ መልክ ነበር እንጂ፡ በሰጦታዎች መመለስ አልነበረም። ነገር ግን ሰባቱንም ቀናት፡ እርሾ የሌለበትን እንጀራ፡ ቃሉን ብቻ ብሉ። እነዚያ፡ ወደ ኋላ ያሉት፡ የሐይማኖት ተቋም የመሠረቱት፡ ሞተዋል። እነርሱ አገዳዎች ናቸው፡ ይሰበሰባሉ ይቃጠላሉም። ሆኖም ሕይወት ቀጥሎ ያልፋል። ታዲያ ምን ይሆናል? በአገዳው፡ በዛላው፡ በገለባው ውስጥ የነበረው ሕይወት በሙሉ፡ በሰንዴው ውስጥ ይጠቀለላል። ሉተርን ያመጣው፡ ዌስሊን ያመጣው፡ ጴንጤቆስጤዎችን ያመጣውም ያው መንፈስ ቅዱስ፡ በትንሣኤ ጊዜ በሙሽራይቱ ውስጥ ይጠቀለላል።

152 "ሰባት ቀን፡ እርሾ የሌለበትን እንጀራ ብሉ።" በሙሽራይቱ መካከል ምንም እርሾ አይገኝም፡ አ—እንዳችም ቃል አይጨመርም፡ ምንም አይኖርም። አስታውሱ፡ በምድር ላይ ላለው ሞት ሁሉ ምክንያት የሆነው አንዲት ቃል ናት፥ እያንዳንዱ ዲቃላ ልጅ የተወለደው ሔዋን፡ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን፡ የመጀመሪያው አዳም ሙሽራ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ተጠራጥራ የሐይማኖት ተቋም የሆነውን፡ ወይም ምሁራዊ የሆነውን፡ ወይም የትምህርት ቤትን ትርጓሜ ሰለተቀበለች ነው፥ ምክንያቱም፡ "በእርግጥ፡ እግዚአብሔር ቸር አምላክ ነው፡" ተብሎ በምክንያት ቀርቦ ነበርና። እግዚአብሔር ቸር አምላክ ነው፡ ሆኖም ጻድቅ አምላክም ነው። ቃሉን መጠበቅ አለብን! ትምህርት ቤትን፡ እርሷ ተቀበለችው።

153 እንዳንዶቻችሁ የሴሚናሪ ልጆች፡ በሕይወታችሁ ጥሪ እንዳለባችሁ ምንም ጥርጥር የለውም፡ ነገር ግን ይህ ትምህርት እንዲወጋባችሁ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ትርጣላችሁ፡ የምትሞቱትም እዚያው ነው... ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ጋር ቆዩ። አይፈቅዱላችሁም፥ ወይም፡ የጉባኤያቸው አባል ለመሆን እንኳ አትችሉም፡ በመድረኩ ላይም አይቀበሏችሁም። ስለዚህ ለእነርሱ ተውላቸው፡ ሙታን ሙታናቸውን ይቀብሩ፡ ቃሉን ክርስቶስን እንከተል።

154 አሁን፡ ሰባት ቀን በሙሽራይቱ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደባለቅ ምንም እርሾ አይኖርም፡ ሰባት ቀን።

155 አሁን አስተውሉ። አሁን ምንም...

> **በዳርቻህም ሁሉ ሰባት ቀን እርሾ ያለበት እንጀራ ከአንተ ዘንድ አይታይም፥...** (እዚህ ጋር ያለው መሰዋዕት ምሳሌ ነው፥ ክርስቶስ ከሆነው መሰዋዕት የምትወጣው ሙሽራ ናት።)... **በመጀመሪያውም ቀን** በማታ **ከሰዋኸው ሥጋ፡ አንዳችም አይኑር፡**...

156 አ—አስታውሱ በቤተ ክርስቲያን ዘመናት ውስጥ እንዴት እንዳለፍን አስታውሱ? የቤተ ክርስቲያን መልእክተኛ ሁልጊዜ የሚመጣው ሌላኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሲሞት ነው፡ ሁልጊዜ። የጴንጤቆስጤ መሞት የሙሽራይቱን መነጠቅ ያመጣል። አያችሁ? የሉተር መሞት ዌስሊን አመጣ። አያችሁ? የዌስሊ መሞት ጴንጤቆስጤን አመጣ። የጴንጤቆስጤ መሞት ደግሞ አሁን መልእክቱን ያመጣል። ይኸው፡ እዚሁ አለ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ውስጥ በንድፍ ተቀምጧል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱ ከሌላው ጋር በትክክል የማይያያዝ አንዳችም ክፍል የለም። አያችሁ? እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች ናቸው። ትምህርት የለኝም፡ ነገር ግን ከተፈጥሮ፡ በሌላ መሰመር ላስተምረው የሚያሳየኝ መንፈስ ቅዱስ አለኝ፥ ያም በቃሉ ነው። ቃሉ መሆን አለበት፡ ነገሮች ተሰፋ ተሰጥቶባቸዋልና።

> ... **ሥጋ፡... በመጀመሪያው ቀን የ**ተሰዋው... **ማታ፡ እስከ ጠዋት ድረስ አያድር።**

157 አሁን፡ እውነትን ይዞ ቤተ ክርስቲያንን “ጻድቅ በእምነት ይኖራል” ብሎ ያስተማረው፡ ሉተር እንኳ። በሜቶዲስት ዘመን፡ ያ ሙሉ ትምህርት ነው ብላችሁ ሙጥኝ ልትሉ አትፈልጉም። ምን ልታደርጉ ይገባል? በእሳት አቃጥሉት። ይህ የምን ምሳሌ ነበር? ከዚያ ቃል የሚወጣው የሐይማኖት ተቋም ገለባ ነው፡ አገዳው፡ ቅርፊቱ፡ በእሳት መቃጠል አለበት። ያለፈበት ያ የሐይማኖት ተቋም ክፍል ሊቀር አይገባውም፡ መሞት አለበት። እ—እስከ ሌላው ዘመን መባቻ ድረስ አታቆዩት፡ አቃጥሉት! አሁን እዚህ እየተናገረ ያለው፡ ለሙሽራይቱ ነው፡ በየዘመናቱ ሁሉ አልፋ ለምትመጣው ሙሽራ ብቻ።

158 “የበጉ ደም፡” ምን ያህል ውብ እንደሆነ አስተውሉ። እነዚህ የክርስቶስ አካል፡ መሰዋዕቱ ናቸው፥ በበሩ ላይ ያለው የበጉ ደም። አሁን፡ አስታውሱ፡ የታረደው በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር።

159 ወይም ብዙ ጊዜ ልንወስድ እንችላለን፡ ነገር ግን የለኝም... እዚህ ለመቆየት ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ቀርተውኛል። ማቆምና ዛሬ ማታ እንደገና መጀመር

ሊኖርብኝ ይችላል፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም በጣም ጊዜ እየወሰድን ነውና። ይህ... እዚህ ጋ በዚህ በአንድ ርዕስ ላይ፡ ሀያ ገጽ፡ ማስታወሻዎች አሉኝ።

160 አሁን ልብ በሉ፡ በዚህ ላይ፡ በ—በጉ በምሳሌያዊ መልክ ክርስቶስ ነበር። ወይስ በትክክል ብዬዋለሁን? ምሳሌ፥ ክርስቶስ በጉ ነበር። እርሱ ወንድ መሆን አለበት፡ ከእናት በግ የመጀመሪያው፥ ወይም ከበጓ፡ በተመቻችሁ መንገድ ጥሩት። የእርሷ የመጀመሪያ መሆን ነበረበት። ነውር ካለበት ለማየትም በመጀመሪያ መፈተን ነበረበት።

161 አሁን፡ ክርስቶስ ተፈትኖ ነበር፥ በጉ በመጀመሪያ ከእናትየው በግ፡ ከድንግል ማርያም መጣ። የተፈተነውም በምንድን ነው? ሰይጣን በቃሉ ላይ። ሔዋንን ሲመታት፡ ወደቀች፥ ሙሴን ሲመታው፡ ወደቀ፥ ዳሩ ግን በክርስቶስ ላይ በበረረ ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስንም በተሳሳተ መንገድ ሊጠቅስለት ሲሞክር፡ ኧ-ህ፡ ያ ሙሴ እንዳልነበረ አወቀ። አያችሁ? ተፈትኖ ነበር። ምን አደረገ... ዞር ብሎም፡ እንዲህ አለው፡ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ **ከ**ሆንክ። አሁን ተአምራትን እንደምታደርግ ነግረውኛል፡ መሲሁም ያንን እንደሚያደርግ ነግረውኛል። አሁን፡ እንደዚያ ከሆነ፡ ተርበሃል፡ አልበላህም፡ እነዚህን ዳቦዎች ወደ፡ ማለትም፡ እነዚህን ድንጋዮች ወደ እንጀራነት ቀይርና፡ ብላ።"

162 እርሱም፡ "'ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡' ተብሎ ተጽፏል" አለው። የሐይማኖት መግለጫችሁ፡ ወዘተ። ዳሩ ግን በምን? በቃል ሁሉ! በከፊል ቃል ነውን? "ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ።" ሰው የሚኖረው በዚያ ነው። አያችሁ? በጉ የወደቀበት የሆነ ሰፍራ እንዳለ ለማየት፡ ተፈትኖ ነበር።

163 ፈሪሳውያንም፡ "ኦ ረቢ፡ አንተ ወጣት ነቢይ፡ ድንቅ እንደሆንክ እናሰባለን። አንተ ቸር ነህ" አሉት።

164 "ለምን ቸር ትሉኛላችሁ? ቸር አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። ያንን ታምናላችሁን?"

165 "ኦህ፡ አዎ። እግዚአብሔር።"

166 "እንግዲያውስ፡ እንደዛ ከሆነ፡ እኔ እርሱ ነኝ።" ኧ-ህ። "ቸር አንድ ብቻ እንደሆነ ተናግራችኋል። አምላክ መሆኔን ሳታምኑ፡ ለምን 'ቸር' ትሉኛላችሁ?" ኧ-ህ። "ታዲያ ለምን ቸር ትሉኛላችሁ? ይህንን እንድታደርጉ ያደረጋችሁ ምንድን ነው? ቸር አንድ ብቻ እርሱም እግዚአብሔር እንደሆነ እያወቃችሁ፡ ይህንን እንድትናገሩ ያነሳሳችሁ፡ ምንድን ነው?"

167 "አንተ የሰውን ክብር ወይም የሰልጣናቸውን ቃል እንደማታከብር እናውቃለን። ያንን እናውቃለን።" ሲሞክሩ... ያንን ግብዝ አውቆት ነበር። አያችሁ?

168 የት እንደቆመ ለማየት ተፈትኖ ነበር፡ አያችሁ፡ በሁሉ መንገድ ተፈተነ፡ እኛ እንደምንፈተነው ተፈተነ። ዳሩ ግን ለእርሱ፡ ፈጽሞ፡ እጅ መሰጠት አልነበረም። በፍጹም፡ ጌታዬ! ያ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር።

169 በጉም ተፈትኖ ነበር፡ ለአሰራ አራት ቀናትም ተጠብቆ ነበር። ያም ሁለት ሰንበታት፡ ወይም ሁለት ዘመናት ነበር። አንደኛው ለአይሁድ ነው፡ እነርሱም በጉን በምሳሌ አቀረቡ፥ ሌላኛው ደግሞ እውነተኛው በግ ላለው፡ ለአሕዛብ

ነው፡ ሁሉም ይህ በግ እንደሚመጣ በማመን ፍጹማን ሆኑ። ነገር ግን እርሱ ለአስራ አራት... ወይም ለአስራ አራት ቀናት ተመረመረ፥ እርሱ ቃሉ ነበረ።

170 የብሉይ ኪዳንን መርምራችሁ፡ "አዲሱን ያወግዛል" ልትሉ ትችላላችሁ። ተሳስታችኋል! ብሉይ ኪዳን ስለ አዲሱ ምስክር ይሆናል እንጂ።

171 በቅርብ ጊዜ አንድ ሰው ሊሞግተኝ ነበር፡ እንዲህም አለ፡ "ምንድነው ችግሩ?" እርሱም፡ "እንዲያውም፡ ከብሉይ ኪዳን ያስተምራል" አለ። ክርስቲያን ሰባኪ፡ ያንን አሰቡት። እንዲህም አለ፡ "ብሉይ ኪዳን ሞቷል አልፏልም።" ኦህ፡ አይደለም! ኦህ፡ አይ! እርሱ ግድግዳው ላይ የተጻፈውን የሚያሳየን፡ ሞግዚት ብቻ ነው። አያችሁ? በትክክል።

172 አሁን፡ አያችሁ፡ ለአስራ አራት ቀናት ተፈትኖ ነበር፡ ያም ክርስቶስ ነበር። አሁን አስተውሉ፡ ከዚያም ሲመሽ ታረደ፡ መታረድም ነበረበት፡ በጉ ነበር። ክርስቶስ በማታ ጊዜ ሞተ፡ ከሰዓት በኋላ። ከዚያም አስተውሉ፡ ከዚያም እርሱ ደግሞ...

173 ደሙ በመቃኑ ላይ መቀባት ነበረበት፡ አያችሁ፡ ደሙም የእንስሳው ሕይወት ነው። "ሥጋውን ትበላላችሁ፥ ዳሩ ግን ሕይወት የሆነውን ደሙን፡ አፍስሱት።" አያችሁ? መሆን ነበረበት... ደሙ መስዋዕቱ ተቀባይነት ባገኘበት ቤት የበር መቃን ጉበን ላይ መቀባት ነበረበት። ክብር! ሕይወት ምንድን ነው? ሰሙ ነው። ያ... እርሱ የሰውን ሰም አስቀመጠ... ወደ በሩ ትሄዳላችሁ፡ ደወሉን ከመደወላችሁ በፊት በበሩ ላይ ምን ሰም እንዳለ፡ ትመለከታላችሁ፡ ታያላችሁ። አያችሁ? በበሩ ጉበን ላይ ደም የተቀባው በውስጥ ያለው መስዋዕት ምን እንደነበር በምሳሌነት ለማሳየት ነው።

174 አሁን በዚያ ደም በኩል አልፈን፡ የትክክለኛውን የአምልኮ ስፍራ፡ በዚያ በኩል እናገኘዋለን። አስተውሉ፡ በበሩ ላይ የነበረው ደም በውስጥ ስለነበረው... ወደ ውስጥ ስለሚሄደው ነገር ሰም ይናገር ነበር፡ እነርሱ እዚያ ውስጥ ነበሩ። የእኛ የአምልኮ ስፍራ፡ በጉ፡ ቃሉ ነው። ያንን እናውቃለን።

175 አሁን፡ ቁጥር 4፡ አስተውሉ፡ "ከእንጀራው ምንም አታስቀሩ፡ ከመስዋዕቱም አንዳችም አታስቀሩ፡" ወይም፡ ከአንዱ ዘመን ወደ ሌላኛው አትውሰዱት።

176 ወደ ኋላ ለመመለስና፡ "እንግዲህ፡ አሁን፡ ሉተራውያን ነን፡ ወደዚህ መምጣት እንፈልጋለን" ለማለት ትሞክራላችሁ፡ ዳሩ ግን በዌስሊ ዘመን ለመወለድ ለሉተር ዘመን መሞት አለባችሁ። በጴንጤቆስጤ ዘመን ለመወለድም በዌስሊ ዘመን መሞት አለባችሁ። በጴንጤቆስጤም ዘመን መሞት አለባችሁ፡ ከእርሱም ምንም ሳታስቀሩ፡ በእሳት አቃጥሉት፡ ምክንያቱም ስንዴው እንደሚወጣበት አገዳ ሊቃጠል ነውና። አገዳው፡ የሐይማኖት ተቋሙ፡ መቃጠል አለበት። ስለዚህ የሐይማኖት ተቋማችሁን ወደ አዲሱ መልእክት ይዛችሁ አትምጡ። አሁን ይህ ቃሉ ነው። የሐይማኖት ተቋም የሆነው ያ አገዳው ነው፥ እርሱ ተሸክሞት ነበር፡ ልክ ነው፥ ዳሩ ግን **ወደዚህ** መጣ፡ ከዚያም አገዳው ሞተ። እርሱ ተሸካሚ ነበረ፡ የሐይማኖት ተቋሙ፡ ነገር ግን ቃሉ በቀጥታ ይቀጥላል። አዎ፡ ቃሉ በቀጥታ ይቀጥላል።

177 አሁን 5ኛውንና 6ኛውን ቁጥር ውሰዱ። አስተውሉ፡ "አይደለም... " አሁን 5ኛውንና 6ኛውን ቁጥር እንውሰድ።

**አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ በደጆችህ በአንዱ ውስጥ፡ ፋሲካን ልትሰዋ አትችልም፥**

178 አሁን አስታውሱ፡ "ከእነዚህ ደጆች በአንዱም ውስጥ አይደለም።" ጌታ እነዚህ የሐይማኖት ተቋማት እንዲኖሯችሁ ይፈቅዳል፡ አያችሁ፡ "እነዚህን ደጆች።"

**ነገር ግን ጌታ... እግዚአብሔር ስሙን ሊያኖርበት በሚመርጠው ስፍራ፡...**

179 በሩ ያ ነው፡ ብቸኛው ስፍራ። "ከእነዚህ ደጆች በአንዱም አይደለም።" ነገር ግን እግዚአብሔር በር አለው።

180 እናንተ፡ "በየጠዋቱ በሜቶዲስት በር እገባለሁ" ትላላችሁ። ያ ቤተ ክርስቲያን ነው። "በየጠዋቱ ወደ ካቶሊክ በር እገባለሁ።" ኧ-ህ። እንግዲህ፡ ጌታ ሕዝቡ በእነዚያ ደጆች ውስጥ እንዲገቡና እንዲወጡ ይፈቅዳል። እግዚአብሔር በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ በሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን፡ በፕሬስባይቴሪያን ቤተ ክርስቲያን፡ በሁሉም ውስጥ፡ በጴንጤቆስጤዎች ዘንድ ሕዝብ አለው። በእርግጥ፡ ዳሩ ግን አት... በዚያ በር ጌታን አታመልኩም። አያችሁ? ነገር ግን ጌታ አንድ የተወሰነ በር አለው። ክብር! በር አለው።

**ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር... ስሙን ሊያኖርበት በሚመርጠው ስፍራ፡ በዚያ... በማታ ፋሲካን** ትሰዋለህ፡...

181 ርብቃ ይስሐቅን መቼ አገኘችው? ኤሊዔዘር ሙሽራ እንድትሆን መቼ ጠራት? በማታ ጊዜ!

> ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡
> የክብር መንገድ በእውነት ይገኛል፡
> በዚያ የውሃ መንገድ ዛሬ ብርሃን አለ፡
> በክቡር በኢየሱስ ስም ተቀብሮ።
> ወጣት ሽማግሌ፡ ሁሉም ንሰሃ ይግባ፡
> መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ እንዲገባ፥
> የምሽቱ ብርሃኖች መጥተዋል፡
> እግዚአብሔርና ክርስቶስ አንድ መሆናቸው ተረጋግጧል።

182 እርሱ የዚያ ጅማሬ ነበረ፡ አሁን እርሷ ወደ ሙሽራይቱ ብርሃን ተሸጋግራለች። ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ?

183 እዚህ ጋ ባቆም ይሻላል፡ ዛሬ ማታ እንደገና እጀምራለሁ፡ ምክንያቱም ይህንን ጥላችሁ እንድትሄዱ አልፈልግም፡ አያችሁ። አይ፡ አይ፡ አሁን የ— የአራት ሰዓት ነው። እንግዲህ፡ እንግዲህ፡ እዚህ ጋ የጻፍኳቸው በጣም ብዙ ማስታወሻዎች አሉኝ። ኦህ፡ ማይ! ዛሬ ማታ ቢሆንስ፡ የተሻለ ይሆናል? [ጉባኤው፡ "አይ፡ አሁን" አለ።—አርታዒ።] እህ? መልካም፡ እናንተ... ጥቂት ወደፊት እንድንገፋ ትፈልጋላችሁ? ["አዎ፡ አሜን።"] እሺ፡ እንግዲያው ጥቂት ወደፊት እንሂድ፡ በጣም በፍጥነት እንፈጥናለን። ይህ እንዴት ነው?

184 አሁን፡ በምኑ እንግባ? "ጌታ አምላክ ከሰጣችሁ ከእነዚህ ደጆች በአንዱም አትግቡ፡ ዳሩ ግን ጌታ ስሙን በሚያኖርበት ደጅ እንጂ።" ወደ ቤቱ አይደለም በ—በር ወደሆነው ደጅ እንጂ። ልክ ነው? እግዚአብሔር ስሙን በበሩ ላይ

ሊያኖር ነው፡ እናንተም አት... ወደ አምልኮ ስፍራ፡ ወደ መቅደሱ የሚያስገባው ደጅ ያ ነው። መሰዋዕታችሁን ይዛችሁ ከእነዚህ ደጆች በአንዱም አትገቡም፡ ዳሩ ግን ጌታ አምላክ ስሙን ሊያኖርበት በሚመርጠው ደጅ ውስጥ እንጂ። አያችሁ?

185 አሁን፡ እርሱ ያንን አድርጓልን? ያ ደጅ የት ነው? በዮሐንስ ወንጌል 10 ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "እኔ ደጁ ነኝ፡ በሩ ነኝ። የእግዚአብሔር ቤት በር እኔ ነኝ። የበጎች በረት በር እኔ ነኝ።" የፍየሎች በረት አይደለም፡ የበጎች በረት እንጂ። አያችሁ? "የበጎች በረት በር እኔ ነኝ። ማንም በዚህ በር ቢገባ፡ ይድናል።"

186 አሁንም በዚህ ላይ ለረጅም ጊዜ ልንቆይ እንችል ነበር። ነገር ግን፡ ጊዜን ለመቆጠብ፡ ወደዚያ የበጎች በረት የሚያስገባው በር እርሱ ነው። አሁን፡ እዚህ ጋር ልብ እንድንል የምንፈልገው፡ ጥላዎችና ምሳሌዎች በትክክል እዚህ በግልጽ ይታያሉ፡ ዳሩ ግን እ... ያንን ገጽ ብወስድ እ... ለጥቂት ጊዜ ያቆያችኋል።

187 እሺ፡ አስተውሉ፡ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በግልጽ እንዲታይ ያደርገዋል። ምክንያቱም ብሉይ ኪዳን በሙሉ የእርሱ ምሳሌ ነውና፡ በዓላቱ ሁሉ፡ አምልኮዎቹ ሁሉ፡ ነገሩም ሁሉ። እንዲሁም እዚህ ጋር፡ በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሥር፡ "አብራራው" ብዬ ጽፌያለሁ። ብዙ ጊዜ የሚወስደውም እዚያ ጋ ነው። በዓላቱ ሁሉ እንዴት... የእህል ቁርባን እንኳ የክርስቶስ ምሳሌ እንደነበር ማብራራት። እስቲ ያንን ብቻ እንውሰድ።

188 አንድ ጊዜ የ—የአገልጋዮች ትምህርት ቤት፡ ወይም የነቢያት ወገን የሚባል ትምህርት ቤት ነበረ። ነቢያትን ያሰለጥኑ፡ ያስተምሩም ነበር። አንድ ጊዜም በእግዚአብሔር-የተጠራ፡ እውነተኛ ነቢይ ሊጎበኛቸው ወጣ። እንግዲህ፡ ለቀድሞው ነቢይ ጥቂት አክብሮት ሊያሳዩት ፈልገው ነበር፡ ስለዚህ ከእነርሱ አንዱ ወጥቶ አተር የመሰለውን አንድ ትልቅ ሰብስብ ለቀመ፥ ዳሩ ግን መርዛማ ቅሎች ነበሩ፡ ሁሉንም በዚያ ሊመግባቸው ነበር።

189 ኦህ! ምን ያህል የሴሚናሪ እቅፎች ነበሩን! አያችሁ? በትክክል። የሆነ ነገር እያበሰሉ ነው። አያችሁ? የሜቶዲስት እቅፎች፡ የባፕቲስት እቅፎች፡ የጴንጤቆስጤ እቅፎች አሏቸው። ሆኖም፡ አያችሁ፡ እነርሱ ከዛፉ ላይ ሊቆረጡ የሚችሉ ዓይነት፡ በላዩ ያደጉ ሁለተኛ ዕድገቶች ናቸው። አያችሁ፡ በዋናው ወይን ግንድ ውስጥ አይደሉም። ሎሚን፡ ባሕረ ሎሚ፡ የመሳሰሉትንም ያፈራሉ፥ ብርቱካን አያፈሩም፡ ዳሩ ግን የብርቱካን ዘር ነን ይላሉ።

190 እንደገና አስተውሉ። አሁን፡ በ—በዚህ ውስጥ፡ ኤልያስ መጥቶ በተመለከታቸው ጊዜ፡ እያንዳንዱን ሊገድል የሚችል መርዛማ ቅሎች መሆናቸውን ባየ ጊዜ፡ "ወዮ፡ በድስቱ ውስጥ ሞት አለ፡" አሉ!

191 እርሱም፡ "አንድ እፍኝ ዱቄት አምጡልኝ" አለ። ዱቄቱንም በውስጡ ጨመረ፡ እንዲህም አለ፡ "አሁን ሰላም ነው፡ የፈለጋችሁትን ብሉ።" ሞትን ወደ ሕይወት ለወጠው።

192 ለክርስቶስም የተሰጠው የእህል ቁርባን... እርሱ የእህል ቁርባን ነበር፡ የእህሉም ቁርባን እያንዳንዱን ትንሿን የዱቄት ቅንጣት አንድ ዓይነት በሚያደርግ በሆነ ወፍጮ መፈጨት ነበረበት፡ ይህም እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው እንደሆነ ያሳያል። በሐይማኖት ተቋማችሁ ውስጥ ብታስገቡት ሕያው

የሚያደርገው ያው አንድ ዓይነት ነገር እርሱ ነው፥ ቃሉ! ክርስቶስ ቃሉ ነው፡ የነገሮች ሁሉ ምሳሌዎች እርሱን ናቸው፥ ታበርናክል፡ የ—የ—የኅብስቱ፡ ሁሉም ነገር። በሳህኑ ሥር ያለው የተቆረሰው ቂጣ የተቆረሰው ሥጋው ነበር፡ አይሁድ ይህን ለምን እንደሚያደርጉት እስካሁን ሊያብራሩት አይችሉም። አያችሁ? እነዚህም ሌሎች ነገሮች ሁሉ የእርሱ ምሳሌዎች ነበሩ።

193 አሁን፡ እንግዲያውስ፡ እርሱን ስንመለከት፡ የሐይማኖት ተቋማትና የሐይማኖት መግለጫዎች ሁሉ ወደ ኋላ ሲቀሩ አሁን እናያለን፥ እርሱ ንጹሕና፡ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ፡ ይህም እርሾ የሌለበት እንጀራ ነው፡ ዮሐንስ ወንጌል 1። በትክክል፡ እርሱ እርሾ የሌለበት እንጀራ ነው። ስለዚህ **ይህንን** ወይም **ያንን** ስትጨምሩ፡ በመጀመሪያ ለእናንተ በተሰጣችሁ ላይ የተጨመረ እርሾ ነው።

194 እዚህ ጋር ተመልከቱ። ዛሬ ዘሩን እየገደለው ያለው ምንድን ነው? ነገሮችን ወሰደው ዲቃላ ያደርጓቸዋል። ስታዳቅሉት፡ ትገድሉታላችሁ። “ኦህ፡ በጣም ያማረ ይመስላል።” እርግጥ ነው! የተዳቀለ በቆሎ፡ የበቆሎ ፍሌክስ፡ ከበቆሎ የሚወጡት ሌሎች የእህል ዓይነቶች ሁሉ። የተዳቀለ በቆሎ፥ ትልቅ፡ እጅግ በጣም ትላልቅ፡ ያማሩ ረጅም አገዳዎች፡ እጅግ ትላልቅ እሸቶች አሉት፡ ከሌላው በእጥፍ የተሻለ ይመሰላል። ነገር ግን ሞት ነው! ሳይንስ እንኳ ያንን ደርሶበታል። አያችሁ? አታዳቅሉት፡ ይገድላችኋል።

195 አሁን፡ እዚህ ጋር፡ ላሳያችሁ። ስሞኑን በግቢዬ ውስጥ ያሉትን አበቦች ውሃ እያጠጣሁ ነበር። እመቤቷም እዚህ በትንሿ ማሰሮ ውስጥ፡ ወይም ከቤቱ ጎን ባለችው ትንሿ መትከያ ላይ አንዳንድ የተዳቀሉ አበቦች ነበሯት። እነዚያን ነገሮች በሳምንት ቢያንስ ሦስት፡ ወይም አራት ጊዜ ውሃ ማጠጣት አለብን፡ አለበለዚያ ይሞታሉ። ዋናው ተክል ግን ውጭ ግቢው ውስጥ ቆሞ ነበር። እዚያ አካባቢ ዝናብ ካልዘነበ ስድስት ወር ሆኖታል፡ ደረቅ ነው… ቢዘንብ እንኳ፡ በአስር ደቂቃ ውስጥ አቧራ ሊቦን ይችላል። ነገር ግን እዚያ ውጭ የሚገኘው ያ ትንሹ ኦርጅናል ተክል፡ ያ ሁሉ ውሃ ከሚጠጣው ከተዳቀለው ተክል ይልቅ እጅግ ያማረና የደመቀ ነው። ውሃውን ብታርቁበት፡ ይሞታል። ነገር ግን እርሱ ውሃውን ከየት አገኘው? ሌላው ነገር ደግሞ፡ ቅማል እንዳይወርሳቸው፡ በየቀኑ ወይም በየሁለት ቀኑ እየተዟዟራችሁ መርጨት አለባችሁ። ካላደረጋችሁ፡ በጣም ለስላሳና ደካማ ስለሆነ፡ ቅማል ይበላዋል። ዳሩ ግን በዚያኛው ኦርጅናል ተክል ላይ የሚወጣ አንዲትም ቅማል የለችም። አይ፡ አይ! ወደ እርሱ ይሳባል ከዚያም ዞሮ ይሄዳል። እርሱ ኦርጅናል ነው! ማዳቀል ምን እንዳመጣ አያችሁ?

196 በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ያለው ያው አንድ ዓይነት ነገር ነው። የሐይማኖት ተቋሙን ከቃሉ ጋር ሊያደባልቁ ይሞክራሉ፡ ይህም… ቃሉ የሐይማኖት ተቋሙ የሚለውን እንዲናገር ለማድረግ ይሞክራሉ። ይህን በምታደርጉበትም ጊዜ፡ እነርሱን መርጨት፡ መንከባከብ፡ ወ—ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲመጡ የወርቅ ኮከቦችንም መስጠት፡ ሌላውንም ነገር ሁሉ ማድረግ አለባችሁ። በትክክል። ዳሩ ግን፡ በእግዚአብሔር ቃል የተወለደ፡ እውነተኛ፡ ዳግመኛ-የተወለደ ክርስቲያን ሲሆን፡ እርሱ ጠንካራ ነው። ያ እናንተ ናችሁ። የዓለም ቅማልና ነገሮች አያስጨንቁትም። እርሱ ንስር ነው፡ በቀጥታ አቋርጦት ይበራል። አያችሁ፡ በሰማያዊ ስፍራ ያንዣብባል። አያችሁ? እርሱ እውነት ነው። ምንም…

197 አስተውሉ። አሁን፡ የሐይማኖት ተቋም፡ የሐይማኖት መግለጫዎች፡ እንዲሁም እርሾ ካለበት እንጀራ የተጨመረ ማናቸውም ነገር እርሾ ከሌለበት እንጀራ ጋር ሊደባለቅ እንደማይችል፡ እዚህ ጋ ልንገነዘብ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስም ወደ እምልኮ በመግባት፡ ቁርባን ውስጥ፡ ምንም እርሾ አብሯችሁ ሊወሰድ እንደማይችል፡ እግዚአብሔርም እርሱን እንደሚቀበል እዚህ ጋ በምሳሌነት ያሳያል።

198 እናንተ፡ "ሜቶዲስት ነኝ" ትላላችሁ። እዚያው ጋ ትሞታላችሁ! "ጴንጤቆስጤ ነኝ።" ትሞታላችሁ!

199 የክርስቶስ ነኝ። በትክክል። በአንድ ነገር ላይ መቆም አለባችሁ። በትክክል። በ—በሆነ ነገር ላይ ቆማችኋል።

200 ቸርችል አንድ ጊዜ ተናግሮ ነበር፡ ሁለት ጣቶቹን ወደ ላይ አነሳና፡ "ድሉን አግኝተናል" አለ። እንግሊዝም በዚያ ቆመች፡ ቸርችልንም አመኑት።

201 ብታምኑም ባታምኑም፡ ዛሬ ጠዋት፡ በአንድ ነገር ላይ ቆማችኋል። ልትኖሩበትና ልትቆሙበት የምትችሉት አንድ ነገር ብቻ ነው፡ እርሱም ክርስቶስ፡ ቃሉ ነው። እውነት!

202 አስተውሉ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከባቢሎን በቀር የሐይማኖት ተቋማትን በምሳሌነት የሚያሳይ ምንም ነገር የለም። ባቢሎንም የተመሠረተችው በናምሩድ ነበር፡ ናምሩድም ዓመፀኛ ነበር። እዚያም ውስጥ ንግስቶቹ ሊሆኑ የተገባቸው፡ ነቢያት የሆኑ፡ የሴቶች ህዝብ ነበረው። ያ የቀድሞው በለዓም እንኳ ከዚያ ክፍል እንደመጣ ያሰባሉ፡ ሰሮችም ነበሯቸው ወዘተ። ያመልኩ ነበር፡ ታውቃላችሁ (የሂስሎፕን '**ቱ ባቢሎንስን፡** የመሳሰሉትንና፡ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የምታነቡ ብዙዎቻችሁ ምሁራን)፡ እንዴትም እ—እንዳደረጉት። **ይህንን** የሚያደርጉ ሴቶችም ነበሯቸው፡ ሴቶችም... አማልክት፡ ሁሉም ነገር ነበራቸው፡ እርሱም አሰገዳጅ ሐይማኖት ነበር። እያንዳንዱ ሰው፡ በባቢሎን ዙሪያ ያለች ከተማ ሁሉ፡ በግንቡ ሥር በናምሩድ ሥር ለማምለክ ወደ ባቢሎን ለመምጣት ተገደው ነበር። አያችሁ? በትክክል። ያንን እንዲያደርጉ ተገደው ነበር፡ ወደ ባቢሎን። ግራ መጋባት የመጣው እዚያ ጋ ነው።

203 ዛሬም ቤተ ክርስቲያን በትክክል እንደዚያው ናት፡ "ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ካልመጣህ፡ **ይህን** ካላደረግህ፡ **ይህን** እንድታደርግና **ይህን** እንድታደርግና **ይህን** እንድታደርግ ልንቀጥርህ ካሰፈለገ፡ ከቦታው ውጭ ነህ።"

204 እዚያ ቱክስን ላሉት፡ ዛሬ ጠዋት ለሚያዳምጡት፡ አንድ ጊዜ... ሰዎችን ሁልጊዜ እገፋፋ ነበር፡ "የትም ብትሄዱ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዱ" እል ነበር። ሕዝቡም ወደ ኋላ ሲያፈገፍግና፡ **ወደዚህ** ሲሄድ አየሁ። እኔም፡ "ችግሩ ምንድን ነው" ብዬ አሰብኩ?

205 ወደ አንዳንዶቹም ሄድኩ፡ "እዚያ በምትሄድበት በመጀመሪያው ቀን፡ 'ቤተ ክርስቲያናችንን ተቀላቀል፡' ብለው ይጠይቁሃል። ይህን ካላደረግህ፡ ተቀባይነት የለህም።" እያችሁ? እያችሁ? እርሱ አሰገዳጅ ነገር ነው፡ በእናንተ ላይ በግድ የሚጫን ነው፡ እያችሁ፡ ያም ባቢሎን ነው። ዳሩ ግን በክርስቶስ ውስጥ፡ የምትገቡት በምርጫ ነው፥ በግድ አይደለም፡ ልባችሁ ወደ ውስጥ ይስባችኋል።

206 እንግዲያውስ እግዚአብሔር ስሙን በባቢሎን አላኖረም። አሁን በጥሞና ተከታተሉ። ስሙን በባቢሎን፡ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሊያኖር አይችልም። ኦህ፡ እነርሱ፡ **እነርሱ** ስሙን እዚያ ውስጥ አኖሩት፡ ዳሩ ግን እርሱ አላደረገውም። አይ።

207 እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ “እንግዲህ፡ አሁን፡ ወንድም ብራንሃም!” ቆዩ፡ ቆዩ፡ ለአንድ ደቂቃ ብቻ ዝም ብላችሁ ተቀመጡ። ጥቂት እንድቆይ ጠይቃችሁኛል። አታዩምን? አሁን አስተውሉ፡ **እነርሱ** ስሙን እዚያ ውስጥ አኖሩት፡ እርሱ ግን አላኖረውም።

208 አሁን፡ እርሱ እንዲህ አለ፡ “ከእናንተ ጋር የምገናኝበትና መስዋዕታችሁን የምቀበልበት ስፍራ ስሜን ላኖርበት የመረጥኩት ስፍራ ነው። የምትገቡትም በዚህ ደጅ፡ ስሜን ላኖርበት በመረጥኩት በዚህ በር ነው። የምትመጡት እዚያ ጋ ነው።”

209 እንግዲህ፡ እነርሱም፡ “ይህች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት” ብለው አስቀመጡ። በዚያ አዋጅ ውስጥ ስህተት የሆነ አንዳች ነገር ቢኖር፡ አንዲት ቃል አስቀርቷል፥ እርሷም “ፀረ” የምትል ናት። ኧ-ህ፡ እርሱ ያስተማረውን ሁሉ፡ እነርሱ ይቃወሙታል። የዘመናችን ፈሪሳውያን።

210 ዳሩ ግን እርሱ ስሙን የት እንዳኖረ ማግኘት አለብን፡ ምክንያቱም ብቸኛው እርሱ ያዘጋጀው ደጅ የሚገኘው በእርሱ ውስጥ ነውና። አሜን! ክብር! ተመልከቱ! ስሙን የት አኖረው? በልጁ ውስጥ።

211 “ኦህ፡” እናንተም፡ “አሁን አንድ ደቂቃ ቆይ፡ ወንድም ብራንሃም። ያ ወልድ ነበር፡ አብ አልነበረም” ትላላችሁ።

212 በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ልጅ ሁልጊዜ የአባቱን ስም ይወስዳል። ወደዚህ ምድር የመጣሁት በብራንሃም ስም ነው ምክንያቱም የአባቴ ስም ብራንሃም ነበርና።

213 ኢየሱስ፡ “በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡ አልተቀበላችሁኝምም” አለ። ለዚህ ላይ ጥቅስ ትፈልጋላችሁን? ዮሐንስ ወንጌል 5፥43። አያችሁ? “በ—በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡ አልተቀበላችሁኝምም።” ስለዚህ አብ “ኢየሱስ፡” የሆነውን የራሱን ስም፡ በወልድ ውስጥ አኖረው። መንገድም እርሱ ነው፡ በሩም እርሱ ነው፡ ቤቱም እርሱ ነው፡ እግዚአብሔር ስሙን ሊያኖር የመረጠበትም እርሱ ነው። እግዚአብሔር ከቶ ስሙን በእኔ ውስጥ አላኖረም፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቶ አላኖረውም፡ በሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ካቶሊክ ውስጥ ከቶ አላኖረውም፡ ዳሩ ግን በተቀባው አማኑኤል በክርስቶስ ውስጥ አኖረው።

214 ስሙም በቃሉ ውስጥ ነው እርሱ ቃሉ **ነውና**። አሜን! ታዲያ እርሱ ምንድን ነው? የተተረጎመው ቃል የእግዚአብሔር ስም መገለጥ ነው። ምንም አያስደንቅም። “ሥጋና ደም ይህንን አልገለጠልህም፡ ዳሩ ግን ማን እንደሆንኩ፡ በሰማያት ያለው አባቴ ይህንን ገልጦልሃል። በዚህም ዓለት ላይ የአምልኮ ስፍራዬን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም ሊያናውጧት አይችሉም።” አሜን! የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ብቻ በጸና መሠረት ላይ ቁሚ። መዝሙሩን ልትዘምሪ ትችያለሽ፡ ነገር ግን ቃል በሆነው በክርስቶስ ላይ ካልሆንሽ፡ የምትንገዳገጂ፡ የምትፍረገረጊ አሸዋ ነሽ። “ዳሩ ግን በዚህ ዓለት ላይ፡” ክርስቶስ፡ “በቃሌ”

215 የሉተርን መልእክት ሠራ፡ እነርሱም የሐይማኖት ተቋም አደረጉት። እያደገ ነበር፡ የእግር መረገጫው። ከዚያም ወደ እግር ክፍሉ፡ ወደ ሜቶዲስት፡ ወዘተ አደገ። ቤተ ክርስቲያኑን የሠራበት ስፍራ እዚያ ጋ ነው፡ በቃሉ ላይ! አሁን፡ እርሱ በሙሉ እግር ወይም በሙሉ ጭን አይደለም፡ እርሱ አካል ነው፥ አሁንም የማጠናቀቂያው ክፍል ላይ ነው። በፒራሚዶች ውስጥ አስተውላችኋል? ሆኖም፡ አሁን፡ የፒራሚድ ሐይማኖትን አልሰብክም።

216 ዳሩ ግን የተጻፈው የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ፡ በሰማይ ላይ የተጻፈ ነበር፡ ዞ-... [ቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] አስተውላችሁታልን? በዞዲያክ ውስጥ የመጀመሪያው ምስል፡ በድንግል ይጀምራል። የመጨረሻው ምስል ደግሞ አንበሳ ነው። በመጀመሪያ በድንግል መጣ፡ ቀጥሎም ከይሁዳ ነገድ እንደሆነው አንበሳ ሆኖ ይመጣል። ከዚያ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ የካንሰር ዘመን፡ ክሮስ ፊሽ፡ ሌሎቹም ዘመናት ሁሉ። በዚህ ውስጥ ለማለፍ ጊዜ ቢኖረን ኖሮ፡ በታበርናክል ግን፡ አድርገነዋል።

217 ፒራ-... ፒራሚዱም እነዚያ መሠረቶች ሆኖ፡ እስከ ንጉሡ ክፍል ድረስ ይወጣል። ሰባተኛውንም ግድግዳ ከማግኘታችሁ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ እዚያ ጋ ትንሽ የማስተዋወቂያ መድረክ አለ፡ በዚያም መልእክተኛው ወደ ንጉሡ ሊያመጣችሁ ይወጣል። (ለንጉሡ፡ ያስተዋወቀውም፡ መልእክተኛ፡ መጥምቁ ዮሐንስ።) ነገር ግን የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ተጠላ። የሰኮን ድንጋይም ይሁን፡ ሌላ ምንም ይሁን ምን፡ አያውቁም፡ የት እንዳለ አያውቁም፡ ምክንያቱም የተጠላ ድንጋይ ስለሆነ ነው። ነገር ግን ሙሉውን ነገር የሚያስረው ያ ድንጋይ ነው፡ ይህም በሙሉ ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ውስጥ ፒራሚዱን ያደርገዋል። ጸጋን ጨምሩ፡ **ይህንን** ጨምሩ፡ **ይህንን** ጨምሩ፡ ሰባት ጭማሪዎች አሉ፡ የመጨረሻው ክርስቶስ ነው። ይህንን **በፍቅራችሁ** ላይ ጨምሩ፡ ጸጋን ጨምሩ፡ በጸጋችሁም ላይ ሌላ ነገር ጨምሩ፡ እስከ ማዕዘኑ ራስ ድንጋይ፡ እስከ ክርስቶስ እስኪደርስ ድረስ ሌላም ነገር ጨምሩ፡ "በሩ እኔ ነኝ።"

218 አሁን፡ ልጅ ሁልጊዜ በአባቱ ስም ይመጣል። ማንኛውም ልጅ በአባቱ ስም ይመጣል። ኢየሱስም፡ "በአባቴ ስም መጥቻለሁ" አለ። ታዲያ የአብ ስም ምንድን ነው? የወልድ ስም ምንድን ነው? እርሱም፡ "ጥቂት ዘመን አለ ዓለምም ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ" አለ። በመንፈስ ቅዱስ መልክ እየመጣ ነው፡ ያም ስም ኢየሱስ ነው። "ኦ ኢየሱስ!" እያሉ ያመልኩ የነበረውም በዚሁ ምክንያት ነው፡ አያችሁ? አያችሁ? አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፥ እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ያ ነው በቃ። "በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡ አልተቀበላችሁኝምም።"

219 አሁን፡ አስታውሱ፡ እዚህ ጋ ደግሞ ጨምሮ፡ "ሌላ ይመጣል፡" የሐይማኖት ተቋም፡ የሐይማኖት መግለጫ። "በስማቸው ይመጣሉ እናንተም ትቀበሏቸዋላችሁ። በፊታችሁ የጸናውን እና የተረጋገጠውን፡ እኔ ቃሉን ግን አትቀበሉኝም።"

220 ያኔ ልክ እንደነበረ፡ ዛሬም እንዲሁ ነው። በዚህ ሕዝብ ዙሪያ ያላችሁ ሰዎች፡ ይህ እንዲያመልጣችሁ! "ሌላ ቤተ ክርስቲያን፡ ይመጣል፡ እናንተም ታምኑታላችሁ፡ ምክንያቱም የፈለጋችሁትን ለማድረግ ስለሚመቻችሁ። እኔ አላጸናውም።" ከተሰጠው መልእክት ውጭ (በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን

ውስጥ) ማናቸውንም ነገር (በማንኛውም ጊዜ፡ ከቶ) አላጸናም፥ የሉተር፡ ጽድቅ፥ የዌስሊ፡ ቅድስና፥ የጴንጤቆስጤ፡ የስጦታዎች መመለስ። በኋላ ላይ... ከእርሱም ውስጥ የሐይማኖት ተቋም እንዳደረጉት ወዲያው፡ እዚያው ሞተ። መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ።

221 ዳሩ ግን እርሱ፡ “ስሜን የማኖርበትን ስፍራ እመርጣለሁ” አለ። ስሙም ኢየሱስ ነበረ። ኢየሱስም ቃሉ ነው፡ ዮሐንስ ወንጌል 1። ልክ ነውን? የአምልኮ ስፍራ ያ ነው፡ ቃል በሆነው በክርስቶስ ውስጥ። “በአባቴ ስም መጥቻለሁ።”

222 ነቢዩም፡ “ስሙ አማኑኤል ይባላል” አለ። ያም ያንን መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ ማቴዎስ 1፥23 ነው። ኢየሱስ፡ ይሖዋ፡ አዳኙ።

223 አሁን፡ 5ኛው ቁጥር እርሱ በሩ እንደሆነ ያሳያል። አሁን ደግሞ፡ በብዙ ሌሎች የማይታዩ ማስረጃዎች፡ ይህ ደጅ፡ ስም፡ እንዲሁም ስፍራ ሊረጋገጥ ይችላል እግዚአብሔር ሰውን የሚያገኝበት የአምልኮ ስፍራ አንድ ብቻ እንዳለ፡ ያም በክርስቶስ ውስጥ ሲሆን ነው።

224 አሁን፡ አሁን ጥያቄው ይህ ነው፡ “በእርሱ ውስጥ እንዴት እንገባለን?” አሁን፡ ይህ ጥቂት ሊቆነጥጥ ይችላል፥ ነገር ግን፡ ታውቃላችሁ፡ ልክ መድሃኒት እንደመውሰድ ነው፡ ካላሳመማችሁ፡ ምንም አይጠቅማችሁም። እያችሁ?

225 አሁን፡ ሉተራውያን በአንድ መንገድ ለመግባት ፈለጉ፡ የሉተርን ቤተ ክርስቲያን በመቀላቀል። ሜቶዲስት እየጮሁ ለመግባት ፈለጉ። ጴንጤቆስጤዎች በልሳን በመናገር ለመግባት ፈለጉ። ያም ገና እርሱ አይደለም! እያችሁ? አይደለም፡ ያ ስጦታዎች ነው፡ ወዘተ። ዳሩ ግን አንደኛ ቆሮንቶስ 12፡ “በአንድ መንፈስ” ይላል። ለዚያ ዘመን ያንን ዘር ለማጽናት፡ ለቃሉ (ለዘሩ)፡ ሕይወት-ሰጭ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ። እያችሁ?

226 እዚህ ጋ የሜቶዲስት-ዘመን ዘር ተኝቶ ነበር፡ ያንን ዘር ወደ ሕይወት ለማምጣት መንፈስ ቅዱስን አስፈለገው ንጹህም... በቅድስና ቤተ ክርስቲያንን ሊያነጻ፥ ሉተር ያንን አልሰበከም፡ ምክንያቱም እያውቀውም ነበርና። ጴንጤቆስጤዎች ለስጦታዎች መመለስ በልሳን ለመናገር ፈለጉ። እያንዳንዱም፡ “እርሱ ነው! እርሱ ነው” ብሎ ያውጃል! እያችሁ?

227 “ዳሩ ግን በአንድ መንፈስ ሁላችን ወደ አንድ አካል ተጠመቅን፡” ያም አካል ቤተሰብ ነው፡ የእግዚአብሔር ቤተሰብ። ያም የእግዚአብሔር ቤት ነው፡ የእግዚአብሔርም ቤት የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። “የጌታ ስም የጸና ግንብ ነው፡ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ይጠበቃል።”

228 አሁን፡ በማዕረግ እንዴት ልትገቡ ትችላላችሁ? ቼካችሁ፡ “ለ—ለተከበሩ፡ ዶክተር፡ አገልጋይ ይከፈል” በማለት እንዴት ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል? እያችሁ? እያችሁ? የተከበራችሁ፡ ዶክተር፡ አገልጋይ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ነገር ግን የጌታ **ስም** “ኢየሱስ ክርስቶስ” ነው። እያችሁ?

229 “ቤተሰቤ እዚያ ከደሙ በታች ስለሚሰበሰብ፡ ስሜን በአምልኮዬ ቤት ደጅ ላይ ላኖር መርጫለሁ፥ ልክ በግብፅ እንደነበረው፡ ውጭ የነበረው ማንኛውም ነገር ሞተ። እዚያም ውስጥ እርሾ ያለበት እንጀራ የለም! የትም ሥፍራ ምንም የሐይማኖት ተቋም ድብልቅ የለበትም፡ ቤቴ! ከዘሮቼ የተወለዱት፡ ልጆቼ!” አሜን! ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን! “ዘሮቼ በእነርሱ ውስጥ ናቸው! የእኔ...

ቃሌን በእነርሱ ውስጥ አኖራለሁ። በልባቸውም ጽላት ላይ እጽፋቸዋለሁ። ያ ቤተሰቤ ነው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ቤተሰብ፥ ቤተሰቡ። በዚህም በር ትገባላችሁ፡ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ወይም ጴንጤቆስጤ አይደለም፡ ነገር ግን ስሜን ባኖርኩበት በር እንጂ።" እርሱ ሜቶዲስት አይደለም። የእግዚአብሔር ስም ሜቶዲስት አይደለም። የእግዚአብሔር ስም ጴንጤቆስጤ አይደለም። የእግዚአብሔር ስም ባፕቲስት አይደለም። የእግዚአብሔር ስም ካቶሊክ አይደለም። እንግዲያው ከደጆቹ ውጭ ቆዩ። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ?

230 "ነገር ግን ስሜን ላኖርበት በምመርጠው ስፍራ።" አሁን፡ እግዚአብሔር ስሙን ያኖረበት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠ ሌላ ስፍራ የለም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ብቻ እንጂ፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ስም፡ የእግዚአብሔርንም ሰብዓዊ ስም የወሰደው የእግዚአብሔር ልጅ እርሱ ነውና። "ልትድኑበት የሚገባ ሌላ ስም ከሰማይ በታች አልተሰጠም።" ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሬስባይቴሪያን፡ የካቴኪዝም ትምህርቶች፡ ወይም ልታደርጉት የምትፈልጉት ሌላም ነገር ቢሆን፡ ግድ የለኝም፥ ጉልበት ሁሉ በሚንበረከክበትና ምላስም ሁሉ እርሱ ጌታ እንደሆነ በሚመሰክርበት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በኩል ብቻ እንጂ። የምትገቡበት መንገድ ያ ነው።

231 በትክክል በውሃ ብቻ ከተጠመቃችሁ በ—በትክክል፡ ከዚያም ቃሉን ከካዳችሁ፡ ዲቃላ ናችሁ፥ አወላለዳችሁ ትክክል አልነበረም። ያኔ እንዳመናችሁት ትናገራላችሁ፡ ሆኖም እርሱን ትክዱታላችሁ።

232 ቤተሰቤን እንዴት ልክድ እችላለሁ? መቼ... ቻርለስ ብራንሃም አባቴ መሆኑን እንዴት ልክድ እችላለሁ? በበሩ ላይ ያለው የደም ምርመራ ያሳየዋል። ኧ-ሀ።

233 ድርጊቴ፡ በሕይወቴም ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል መጽናቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔን ወይም አለመሆኔን ያሳያል። አሁን፡ የእግዚአብሔር ብቸኛ ስፍራ ያ ነው። አያችሁ? እግዚአብሔር መሰዋዕታችሁን የሚቀበልበት ብቸኛው ስፍራ (ምንም ያህል ቅን ብትሆኑም ግድ የለኝም) በክርስቶስ ውስጥ ነው።

234 አስታውሱም... እንዲህ ትላላችሁ፡ "እንግዲህ፡ አምኛለሁ፥ ገብቻለሁም፡ ጭምር።" አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል... እንዲህም ትላላችሁ፡ "እንግዲህ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ 'ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ፡ ድኗል፡ ይድናልም' ይላል።"

235 ያንን ይላል፡ ሆኖም **እንዲህ**ም ተብሎ እንደተጻፈም አስታውሱ፡ **እንዲህም** ተብሎም ተጽፏል፡ "በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር፡ ማንም ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ሊል አይችልም።" አያችሁ? "እርሱ ነው" ልትሉ ትችላላችሁ፡ ዳሩ ግን ለቃሉ ሕይወትን የሚሰጠው፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ መሆናችሁን በማጽናት እስካላረጋገጠው ድረስ እርሱ አይደለም። ያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

236 "ስሜን ላኖርበት የመረጥኩት ስፍራ። በሌላ በማናቸውም ደጅ አታመልኩም፡ ዳሩ ግን ስሜን ባኖርኩበት ደጅ ውስጥ እንጂ፥ ያኔ እቀበላችኋለሁ፡ በቤተሰቤ ውስጥ ናችሁ።"

237 አሁን፡ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የቤተሰቡን አባት ትእዛዝ ያከብራል። “እርሱም የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት ነው፥ ለግዛቱም ለንግሰናውም ፍጻሜ የለውም፡ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል።” እርሱም ገዥ፡ ንጉሥ፡ አማኑኤል፡ ፊተኛው፡ ኋለኛው፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት በመሆኑ፡ ልጆቹ ሁሉ እያንዳንዱን ቃል እስከ ትእዛዙ ድረስ ይታዘዛል ምክንያቱም የእርሱ ክፍል ናቸውና።

238 እኛ በቤታችን ውስጥ ልክ ብራንሃሞች እንደሚኖሩት እንኖራለን። እናንተ በቤታችሁ፡ ጆንሶች፡ ልክ ጆንሶች እንደሚኖሩት ትኖራላችሁ።

239 በእግዚአብሔርም ቤት ውስጥ በእግዚአብሔር ቃልና ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንኖራለን፥ ሌላውንም ማናቸውንም፡ አታላይ፡ አናዳምጠውም። አያችሁ? “እርሾ የሌለበትን እንጀራ፡ እያንዳንዱን የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ልክ እንደምሰጣችሁ ትበላላችሁ።” ዳሩ ግን ወደ ኋላ ለመመለስና ያንን በዚህኛው ውስጥ ለመውጋት አትሞክሩ፡ ምክንያቱም ወደ አገዳነት መጥቷልና። “ከመሰዋዕቱ የተረፈውን አጥንትና ነገሮች ወስዳችሁ ታቃጥሏቸዋላችሁ!” አልፏል፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመን ሞቷል፡ አልፎ ሄዷል፥ አሁን እኛ በሌላኛው ውስጥ ነን። አሜን!

240 “ስሜን ላኖርበት **እኔ** የመረጥኩት ስፍራ።” ኦህ፡ ማይ! አንደኛ ቆሮንቶስ 12።

241 አስተውሉ፡ ኤፌሶን 4፥30።

> **... ለቤዛችሁ ቀን የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ**፡ እስከ... (ቀጣዩ መነቃቃት? )... **እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ።**
>
> **... ለቤዛችሁ ቀን የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ።**

242 አሁን አስተውሉ። ያንን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታችን እናውለው። ከዚያ ብንሄድ ይሻላል፥ ሕዝቡን እያደከምኩ ይመስለኛል። አያችሁ? [አንድ ሰው፡ “አይ፡ አይደለህም፡ ወንድም ብራንሃም” አለ።—አርታዒ።] እዚህ ጋር ተመልከቱ፡ ሰዎች እየተነሱ ወደ ቤታቸው እየሄዱ ነው፡ አያችሁ፡ ስለዚህ እራት ማ—ማብሰል ይኖርባቸዋል፡ ሊያገኙት የሚፈልጉትም ሰው ይኖራል። እዚህ መጥተው ቀኑን ሙሉ ለማዳመጥ አልጠበቁም ነበር። አያችሁ? ነገር ግን፡ ተመልከቱ፡ ታውቃላችሁ...

243 [ወንድም ቤን ብራያንት፡ “እኛ ግን፡ ጠብቀን ነበር” አለ።—አርታዒ።] ቤን፡ ኦህ፡ አንተ ላይ መሥራት ይገባኛል! ተባረክ! አመሰግናለሁ፡ ወንድም ቤን። እወድሃለሁ፡ ወንድም ቤን።

244 ያ ልጅ በዚያ ጦርነት ውስጥ ስለ እኛ ምን ያህል መከራ እንደተቀበለ ብታውቁ ኖሮ፥ በጥይት ተበሳስቷል፡ በፍንዳታም ተመቷል፡ ሌላውንም ነገር ሁሉ ሆኗል። ሁሉንም ነገር ያለፈበት ሕይወት ነበረው፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ባርኮታል። እውነተኛ ሆኖ ጸንቷል። ሚስቱ ትታው ሄደች፡ ኮበለለች፡ ዳግመኛም አገባች፡ ልጆቹንም ወሰደችበት። ኦህ፡ ማይ፡ ስለ እርሱ ማሰብ እንኳ አልችልም።

245 ሆኖም፡ ያም ሆነ ይህ፡ እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ቤን።

246 እርሱ አሁን ነርቮቹንና ሌላውንም ነገር ሁሉ እየተጫነው፡ በሰውነቱ ውስጥ የቦምብ ሰብርባሪ ሞልቶት ተኝቷል። እንግዲህ፡ የነገሮችን የጀርባ ታሪክ ማወቅ አለባችሁ፡ አያችሁ። እግዚአብሔር ያንን ልጅ ይባርከው። አዎ።

**... ለቤዛችሁ ቀን የታተማችሁበትን።**

247 አስተውሉ! አሁን፡ ይህ ጥቂት ሊቆነጥጥ ይችላል፡ ነገር ግን አስተውሉ። ከእኔ ጋር አትጣሉ። ብቻ አስታውሱ።

248 እስራኤል አንድ ጊዜ ያንን በር፡ በበሩም ላይ ያለውን ያንን ደም፡ ሰሙን (ደሙን፡ ሕይወቱን) በተመለከተ ጊዜ፡ ከዚያም ደም በታች ከገባ በኋላ፡ ከግብፅ እስከወጡበት ጊዜ ድረስ ዳግመኛ ወደ ውጭ አልወጡም።

> ... የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ፡ **በእርሱም** ወደ ውስጥ ከገባችሁ በኋላ ተመልሳችሁ እስክትዋጁ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ውጭ አትወጡም። (አያችሁ? )

249 ታውቃላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ ትክክል ነው። እርሱ እዚያ ውስጥ ቃላትን ያሰቀምጣል፡ የቤዛነትን ሙሉ ሰዕል ለማምጣት፡ በሚሄድበት ስፍራ፡ ልታስቀምጡት ይገባል። አያችሁ? አያችሁ?

> **... እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ።** (እስክትዋጁ ድረስ።)

250 እዚያ ውስጥ ታትማችኋል፡ ከደሙም በታች ናችሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ውጭ አትወጡም። ታዲያ እናንተ ምንድን ናችሁ? በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ያላችሁ የእግዚአብሔር ልጅ ናችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስም ታትማችኋል። ዲያብሎስ ሊያገኛችሁ ቢፈልግ እንኳ አይችልም፥ ምክንያቱም ሞታችኋል፡ ያ የቀድሞው ባላችሁ ሞቷልና፥ ተቀብራችሁማል፡ ሕይወታችሁም በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ውስጥ ተሰውሯል፡ በመንፈስ ቅዱስም ታትሟል። አያችሁ? እንዴት ሊያገኛችሁ ይችላል? እንዴትስ ወደ ውጭ ልትወጡ ትችላላችሁ? እዚያው ናችሁ! ክብር ይሁን! አሁን ይህንን እተወዋለሁ፥ ሰለምን እየተናገርኩ እንደሆነ እንድታውቁ ያህል ብቻ ይበቃል።

251 ከዚያም አዲስ ፍጥረት፡ ለሐይማኖት ተቋም ሳይሆን ለቃሉ የተፈጠረ ናችሁ። እናንተ የቃሉ ፍጥረት ናችሁ። ምክንያቱም የመሠረቱ ድንጋይ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በእናንተ ውስጥ ተጥሎ ነበርና፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንድትሆኑ አስቀድማችሁ ተወሰናችኋል።

252 በዚህም ላይ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ይመጣል፡ በእያንዳንዱ ዘመን፡ ወደ ላይ የሚወጣውን ያንን ቃል ለማጽናት፡ ልክ ኢየሱስ በዘመኑ እንዳደረገው፡ እርሱም የሁሉ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ነው። እያንዳንዱ ዘመን በእርሱ ውስጥ ተቀምጦ ነበር። በኢየሱስ ውስጥ ሙሴ ነበረ። በኢየሱስ ውስጥ ዳዊት ነበረ። በኢየሱስ ውስጥ ነቢያት ነበሩ። ልክ ነውን? ዮሴፍን ተመልከቱ፡ ወደ ሰላሳ በሚጠጋ የብር ቁርጥራጭ ተሸጦ፡ ጉድጓድ ውስጥ ተጥሎ፡ እንደሞተ ተቆጥሮ፡ ከዚያ ወጥቶ፡ ሄዶ በፈርዖን ቀኝ ተቀመጠ። ተመልከቱ፡ በትክክል፡ ኢየሱስ ነበረ... ዮሴፍ በኢየሱስ ውስጥ ነበረ።

253 እርሱም በመጣ ጊዜ፡ የነገሥታት፡ የነቢያት (ሃሌሉያ) ሙላት ነበረ፡ የመለኮት ሙላት በሰውነት በእርሱ ውስጥ አደረ። እርሱ የመጣው ከዚያ ውስጥ ሙሽራን፡ አውራ ሥራን ሊዋጅ ነው። ለሰይጣን እንዲህ የምትል አውራ ሥራ...

254 እርሱ፡ "የተአምራት ዘመን አልፏል። የምታወሩት ነገር እንዲህ የሚባል ነገር የለም" ሲል።

255 "ወደ ኋላዬ ሂድ፡ ሰይጣን።" አያችሁ? አያችሁ፡ አውራ ሥራ ቆማ ሰትጠብቅ።

256 አንድ ቀን የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ይመለሳል፡ የሁሉ ራስ፡ ሙሽራይቱንም ወደ ራሱ ይቀበላል፥ ሴትም ከወንድ ተወስዳለችና፡ የወንድ ክፍል ናት። እያንዳንዱ... የወንዱ ዘር በሴቲቱ ውስጥ አለ፡ ሴት የሚያደርጋትም ያ ነው። የእግዚአብሔርም ቃል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው በዚህ መንገድ ነው፡ ቤተ ክርስቲያኒቱን ሙሽራ የሚያደርጋት ያ ነው። የሐይማኖት ተቋም አይደለም፡ ያ ከዲያብሎስ ነው፡ እያንዳንዳቸው። እዚያ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያንን እያልኳቸው አይደለም፥ እነርሱ ምስኪን የተታለሉ ሰዎች ናቸው፡ ኢየሱስ፡ "ዕውር ዕውርን እንደሚመራ" እንዳለው ነው። ሊጠራቸውም አልቻለም።

257 እነርሱም፡ "እንዴት፡ አንተ ከዝሙት የተወለድክ ነህ! ወደ አንተ እንደሚመጡ ማን ነገረህ? የትኛው ትምህርት ቤት፡ የትኛው ሴሚናሪ ዕውቅና ሰጠህ" አሉ? እንዲህ አሉትም፡ "እኛ ሙሴ አለን። እናውቃለን... "

258 እርሱም፡ "ሙሴን ብታውቁት ኖሮ፡ ባወቃችሁኝ ነበር" አለ።

259 ምክንያቱም ሙሴ በአራቱ መጻሕፍቱ ስለ እርሱ ጽፏልና፡ "ጌታ አምላካችሁ ቃሉን የሚሰጥ፡ ወይም፡ እንደ እኔ ያለ፡ ነቢይ ያስነሳላችኋል፡ ያንን ነቢይ የማይሰማም ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጠፋል።" ያለው ነገር ያ ብቻ ነው። ታዲያ እርሱ ምንድን ነው? ቃሉ። እርሱስ ምንድን ነው? አንዳችም እርሾ አታሰቀሩ በ... በ... በእርሱ ውስጥ አንዳችም እርሾ አታስገቡ። ምንም የሐይማኖት መግለጫም ሆነ፡ የሐይማኖት ተቋም አትጨምሩ፡ ምክንያቱም እዚያው ጋ ስለሚረክስ፡ መሰዋዕታችሁ ተጠናቅቋል።

260 ሄዳችሁ መብላት እንድትችሉ፡ አሁን በጣም፡ እንፍጠን።

261 አስተውሉ! አሁን፡ እንግዲህ፡ እናንተ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያላችሁ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፡ የእግዚአብሔርም አስተዳደር አካል ናችሁ። ሮሜ 8፥1፡ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።" ምክንያቱም ለዓለም ሞተዋል፡ በእርሱ ግን ሕያዋን ናቸው፡ በዚህም በአሁኑ ዘመን በመኖር፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነላቸውን ቃል፡ እውን እያደረጉ፡ ስማቸውንም በዚህ በሙሽራይቱ መጽሐፍ ውስጥ አስፍሯል። ውሃውም በልብ ውስጥ ባለው በዚያ ዘር ላይ ሲወርድ፡ ወደ ክርስቶስ ሙሽራነት ከፍ ያደርገዋል። ኦህ፡ ማይ! ሊሆን በሚችለው መጠን ፍጹም ነው። በየዘመናቱም ሁሉ እንደዚሁ ነበር።

262 ሉተራውያን፡ በመጽደቅ ሥር፡ እግሮቹ፡ እንደዚያው ከፍ አደረጉት፥ ዌስሊ፡ በመቀደስ ሥር። የጴንጤቆስጤዎችም በክንዶች ሥር፡ ሰራዎችና ድርጊቶች እንዲሁም ሌሎችም፡ ካልቪኒስቶች መሆን ነበረባቸው... ወይም አርሚኒያኖች

መሆን ነበረባቸው፡ ሕጋውያን መሆን ነበረባቸው። ነገር ግን አሁን ወደ ራሱ፡ ወደ መደምደሚያው ድንጋይ መጥተናል። የመደምደሚያውም ድንጋይ "ጸጋ! ጸጋ!" ብሎ ጮኸ።

263 የመደምደሚያውም ድንጋይ ምን ብሎ ይጮኻል? "ጸጋ! ጸጋ!" ከሞትና ከየሐይማኖት መግለጫ አልፎ፡ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ሕያው ቃል ተሻግሯል። እግዚአብሔር ለዘመኑ ያዘጋጀው ብቸኛው እቅድ፡ በቃሉ ዘመን ያሉ ልጆቹ ሕያው እንዲሆኑ ከአንድ ነገር ላይ እንደተለኮሰ ብልጭታ በመንፈስ የነቁ ናቸው፥ አሁንም በሰማያዊ ስፍራዎች ተቀምጠዋል (በአሁን ጊዜ)፡ ቀድሞውኑ ሕያዋን ሆነው በቃሉ ውስጥ ላለ እያንዳንዱ ተስፋ ተገዢዎች ናቸው። ታዲያ ያ ምን ያደርጋል? እናንተ የእግዚአብሔር ዘር አካል፡ የቃሉ አካል በመሆናችሁ፡ ሌሎች ሰዎችም የእግዚአብሔር ቃል አካል ሆነው፡ አብረው በመቀመጥ፡ ሙሉውን የክርስቶስን አካል ይገልጣሉ፡ ምክንያቱም በመካከላችሁ እርሾ የለምና። (ሰለ ምን እየተናገረ እንዳለ አያችሁ፡ ወንድም ብራውን? ) በመካከላችሁ ምንም እርሾ የለም፡ ቃሉ ብቻ እንጂ፡ በሰማያዊ ስፍራዎች ተቀምጦ፡ ሰሙን ባኖረበት በር ላይ፥ እርሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

264 በመካከላችሁ እርሾ አለመኖሩ፡ የመለኮትን ሙላት በሙሉ በአካል በመካከላችሁ ያመጣዋል። በሉተር ዘመን ይህን ማድረግ አልተቻለም፡ በዌስሊ ዘመን ይህን ማድረግ አልተቻለም፡ በጴንጤቆስጤ ዘመንም ይህን ማድረግ አልተቻለም፥ ነገር ግን የሰው ልጅ በሚገለጥበትና፡ ግልጽ በሚሆንበት ቀን፡ ቤተክርስቲያንን ከሙሉ የእግዚአብሔር አምላክነት ጋር በሕዝቡ መካከል መልሶ በማምጣት፡ እነዚያኑ የሚታዩ ምልክቶችን እያሳየ፡ በመጀመሪያ በምድር ላይ በነቢይ-አምላክ መልክ በተገለጠ ጊዜ እንዳደረገው ራሱን ይገልጣል። ኦህ! ክብር! በሚልክያስ 4 የተሰጠ ተሰፋ፡ በቀሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም የተሰጠ ተሰፋ ነው። የት ነው የምታመልኩት? በእግዚአብሔር ቤት፡ ተቀምጣችሁ (በአሁን ጊዜ)።

265 አሁን፡ በፍጥነት፡ እስቲ አሁን በጣም ፈጠን ብለን እንመልከትና፡ ከዚያም እንቀጥላለን... ጌታ ቢፈቅድ፡ በአሰር ደቂቃ ውስጥ እንሄዳለን።

266 አሁን በዘመናቸው፡ ወደዚህ የእግዚአብሔር ቤት ሕያው የሆኑትን አንዳንዶቹን እንመልከት።

267 ሄኖክ! (በአሰር ደቂቃ ውስጥ እንጨርሳለን፡ ያን ያህል ጊዜ ብቻ መታገስ ከቻላችሁ።) ተመልከቱ፡ ሄኖክ በዘመኑ የነበረው ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ነበረ፡ ነቢይ ነበረ።

268 ነቢይ የእግዚአብሔር አንጸባራቂ ነው። ሰንቶቻችሁ ይህንን ታውቃላችሁ? አ—አንጸባራቂው ራሱን አያንጸባርቅም፡ አ—አንጸባራቂው ነጸብራቁ አይደለም። እንዲያንጸባርቅ አ—አንጸባራቂውን የሚመታው ነገር መኖር አለበት። ሰለዚህ ነቢይ ምንም ነገር ሊያንጸባርቅ የማይችል ዳሩ ግን የክርስቶስን መልክ የሆነውን ቃሉን፡ ለማንጸባረቅ ከነጸብራቁ፡ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መሰመር ላይ ያለ፡ የእግዚአብሔር የተመረጠ ዕቃ ነው። አያችሁ፡ ሌላ ምንም ነገር ይህንን ሊያደርግ አይችልም። እናንተ አንጸባራቂ ናችሁ፡ ነቢዩ መጽሐፉን መብላት የነበረበት ምክንያትም ይሄው ነው። ጥቅልሉን መብላት

የነበረበት ምክንያት ይሄው ነው። ለዚያ ዘመን ያንን ቃል ማንጸባረቅ ነበረበት። ገባችሁ?

269 ሄኖክን ልብ በሉ፡ በምሳሌ የእግዚአብሔር ፍጹም አንጸባራቂ ነበረ። እግዚአብሔር በ—በእርሱ ከተጠቀመበት በኋላ ሲጨርስ፡ ወዲያውኑ ለወተው፡ ወደ ላይም ወሰደው። ያንጸባረቃቸው ሜካኒክስ በመንፈስ ዳይናሚክስ ሆነው፡ ወደ ላይ ወሰዱት።

270 በኤልያስ ዘመንም እንዲሁ ነበር። ኤልያስ፡ እስከ አጥንቶቹ ድረስ እንኳ፡ ያ ነጸብራቅ ባለበት... በሰውነቱ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል የተገለጠ በማድረግ የእግዚአብሔር አንጸባራቂ ነበር። የሞተን ሰው በላዩ ላይ አኖሩ፡ ዳግመኛም ሕያው ሆኖ ተነሳ። እኛ የክርስቶስ ሙሽራ እስከሆንን ድረስ፡ የእርሱ ሥጋና አጥንት ነን። ይህንን ታምናላችሁ? መልካም። እርሱ ስለ እኛ ሞተ፡ ለራሳችንም ሞተን በሰሙ ተቀበርን፡ ይኸውም "ከእንግዲህ ወዲህ የዓለም ሳንሆን፡ ነገር ግን በእርሱ እንድንሆን" ነው፡ በሰማይም ያለው ሁለቱ ቤተሰብ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠርቷል። ያም ኤፌሶን 1፥21 ነው። ሁለቱም በሰማይ... በሰማይ ያለው ቤተሰብ። በሰማይ ያለው ቤተሰብ ሰሙ ማን ተባለ? ኢየሱስ። በምድር ያለው ቤተሰብ የተሰየመው በማን ነው? እንግዲህ፡ ያም ደሙ ያለበት፡ የእግዚአብሔር ቤት ነው። ልክ ነው? ያ ደጁ ነው፡ ያ በሩ ነው፡ ያ ሰሙን ያኖረበት ስፍራ ነው፡ ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ። እናንተ በምትኖሩበት ዘመን የሚያንጸባርቀውና የሚፈነጥቀው ቃሉ ነው። እርሱ የነበረው እንደዚያ ነው፡ ሙሴም እንደዚያ ነበረ፡ ያዕቆብም እንደዚያ ነበረ፡ ሌሎቹም ሁሉ እንደዚያ ነበሩ፡ ያንን የእግዚአብሔር ቃል የሚያንጸባርቁ፡ እግዚአብሔር ራሱን የሚያንጸባርቅበት አንጸባራቂ ነበሩ። ወደዚያም ፍጹም ወደሆነው የእግዚአብሔር መልክ፡ የእግዚአብሔር አውራው ሥራ ወደሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መሆን መጣ፡ እርሱም አንጸባራቂዎች የነበሩትን ሌሎችም ለሙሽራነት ይወስዳቸው ዘንድ ተመታ።

271 ሙሴ በእርሱ ውስጥ ነበረ። ኢያሱ በእርሱ ውስጥ ነበረ። በእርሱ ውስጥ ከሆናችሁ ደግሞ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በእርሱ ውስጥ፡ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆናችሁ ነበራችሁ፥ ከእርሱ ጋር መከራን ተቀበላችሁ፡ ከእርሱ ጋር ሞታችሁ፡ ከእርሱ ጋር ወደ መሰቀል ወጣችሁ፡ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ፥ አሁንም የዘመኑን መልእክት ለዓለም እያንጸባረቃችሁ፡ በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጣችሁ፡ የዓለም ብርሃን ሆናችሁ፡ አሁንም ከእርሱ ጋር ናችሁ። "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፡" ዳሩ ግን በየሐይማኖት ተቋም እንቅብ ከተሰወረ፡ እንዴት ሊያዩት ይችላሉ? በትውፊቶቻችሁ ምክንያት፡ ብርሃኑን ከንቱ ታደርጋላችሁ! በመሞከር... እናንተ የሐይማኖት ተቋም ሰዎች፡ ብርሃኑን ከቤተክርስቲያናችሁ ለማራቅ በመሞከር፥ አትገቡም፡ እነርሱም እንዲገቡ አትፈቅዱላቸውም። አሜን።

272 እዚህ ጋር እናቁም። ማይ፡ እዚህ ጋር ብዙ ነገር አለኝ። ል—ልንቀጥል እንችል ነበር... ኦህ፡ ማይ! አምስት ደቂቃ ብቻ ነው ያለን።

273 በሩ ማን እንደሆነ አያችሁ? እግዚአብሔር ሰሙን የት አኖረ? በኢየሱስ ውስጥ። ወደ ሰሙ እንዴት ትገባላችሁ? ወደዚያ እንዴት ትገባላችሁ? በዚያ

ውስጥ በመጠመቅ ነው! እንዴት? በውሃ? በመንፈስ! “አንድ ጌታ፡ አንዲት ሃይማኖት፡ አንዲት ጥምቀት።” ያ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው።

274 የውሃ ጥምቀት ክርስቶስን መቀበላችሁን እንዳሳወቃችሁ፡ ከሰዎች ጋር ኅብረት እንድታደርጉ ብቻ ነው የሚያደርገው። ያ እውነት ነው። ዳሩ ግን የመንፈስ ጥምቀት ነው የሚያስፈልገው። የኢየሱስን ስም በእናንተ ላይ ጠርቼ ላጠምቃችሁ እችላለሁ፡ ያ ግን እውን አያደርገውም።

275 ዳሩ ግን አንዴ ያ መንፈስ ቅዱስ... እውነተኛው ቃል ወደ እናንተ ውስጥ ሲገባ (ቃሉ፡ ኢየሱስ)፡ ያኔ፡ ወንድሜ፡ መልእክቱ ከእንግዲህ ለአንተ ምስጢር አይሆንም፥ ታውቀዋለህ፡ ወንድሜ፡ በፊትህ ሁሉ ነገር በርቷል። ሃሌሉያ! ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን! አሜን!

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
እርሱ አስቀድሞ ወዶኛልና
መዳኔንም ስለገዛልኝ...

ውድ አምላክ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ሰዎች እንድትፈውስ፡ እያንዳንዳቸውንም ጤነኛ እንድታደርግ እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

276 ኦህ! ፍቅር! ኦህ!

በእምነት ያንን፡ ከአንተ የሚፈስው ቁስል
የሚያመነጨውን ጅረት ካየሁበት ጊዜ ጀምሮ፡ (ከዚያ
አውራ ሥራ።)
የሚቤዥ ፍቅር መዝሙሬ ሆኖአል፡

277 እንዴት ትችላላችሁ... ? እግዚአብሔር ፍቅር ነው። “የሚወድ ከእግዚአብሔር ነው፡” መለኮታዊ፡ ቅዱስ ፍቅር፡ ቆሻሻ ፍቅር አይደለም፥ ንጹህ፡ ጥርት ያለ፡ ቅዱስ ፍቅር፡ ቃል የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር። “በአንተ ላይ ኃጢአት እንዳልሠራ፡ ሕግህን በልቤ ሰወርሁ፡” ኦህ፡ ማይ፡ ያ ዳዊት ሲጮህ ነው። እርሱ ድንቅ አይደለምን? አትወዱትምን?

278 አሁን፡ መንገድ አለ፡ ንጹህ፡ ቅዱስ መንገድ፡ እግዚአብሔር እናንተን የሚገናኝበት ብቸኛው መገናኛ ስፍራ። “እግዚአብሔር ሆይ፡ አሁን፡ ጥሩ ሜቶዲስት ነኝ። ጥሩ ባፕቲስት ነኝ። ጥሩ ጴንጤቆስጤ ነኝ፡” ስላላችሁ አይደለም። አይደለም! ቃል በሆነው በኢየሱስ ውስጥ፡ ዛሬ **ለዚህ** ዘመን መልእክት፡ እየተገለጠ ባለው የቃሉ ክፍል ውስጥ ስላላችሁ ነው፥ የሉተር፡ የዌስሊ፡ ጴንጤቆስጤ አይደለም፥ ዳሩ ግን የእናንተ ኢየሱስ፡ **ወደዚህ** የመጣው፡ ነጸብራቁ ነው። **ወደዚያ** ወደ ኋላ መመለስ አትችሉም፡ ያ በቅዱስ እንጀራችሁ ላይ እርሾን መጨመር ነው፡ ይኸውም፡ “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ፡ በየወቅቱ ይኖራል።”

279 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ታላቁ የማዕዘን ራስ፡ ና። እዚያ ማዶ ወድቆ ተመልከቱ፡ በሰማዕትነት ያለፉት የነዚያ ሉተራውያን ትቢያ፥ እነዚያን ሜቶዲስቶች ተመልከቱ።

280 እነዚያን ጴንጤቆስጤዎችና የመሳሰሉትን፡ አሁን እየመጡ ያሉትን፡ ያንን የወጣውን እውነተኛ ዘር ተመልከቱ።

281 እናንተ የአሴምብሊ ኦፍ ጋድ ሰዎች ሄዳችሁ ተደራጃችሁ፡ እግዚአብሔር ካወጣችሁ ከዚያው ነገር ላይ፡ አሳማ ወደ ጭቃው እንደሚመለስ ወደ ኋላ ተመለሳችሁ።

282 እናንተ ዋንነስ፡ ዩናይትድ፡ የቀድሞ ጄ.ሲ.፡ የ... ኢየሱስ ክርስቶስ የጴንጤቆስጤ አሴምብሊስ ማኅበራት ሁሉ። አንዱ ለጥቁሮች ሆነ፡ በዘር መድልዎ ምክንያትም ራሳችሁን ለያችሁ። ያንን ያደረጋችሁ፡ ከዚያም ራሳችሁን አንድ አድርጋችሁ “ዩናይትድ” ብላችሁ የጠራችሁ። ከዚያም ተደራጃችሁ፡ በአሴምብሊስም ላይ ተነጫነጫችሁ፥ “ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ።” ትፋቱ በመጀመሪያውኑ ውሻውን ካሳመመው፡ ዳግመኛ አያሳምመውምን? አመጋገባችሁን ከየሐይማኖት ተቋማችሁ ወደ ቃሉ ለውጡ፡ ከክርስቶስም ጋር ኑሩ። ታሳፍራላችሁ!

> አባት አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
> አባት አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
> አባት አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
> ከአድማስ ተሻግሮ።
>
> አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
> አንድ ብሩህ ቀን... እየዋለሁ፡
> አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
> ከአድማስ ማዶ።
>
> ኦህ፡ እንዴት ያለ አስደሳች ስብሰባ ይሆናል!
> አይደል... (ቃል ይቀድማል!)... ስብሰባ!
> (ሙሽራይቱ ስትወጣ፡ ቃል በቃል።)... መልካም ስብሰባ!
> ከአድማስ ማዶ።
>
> ኦህ፡ አንዷ ቀን ነገ ትሁንልኝ፡
> አንዷ ቀን ነገ ትሁንልኝ፡
> አንዷ ቀን ነገ ትሁንልኝ፡
> ከአድማስ ማዶ።

283 እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ “ያንን ማለትህ ነውን፡ ወንድም ብራንሃም? ”

284 አዎ፡ ወዳጄ! የዚያ ዘመን ሉተራውያን፡ የዘመናቸው ዌስሊዎች፡ የዘመናቸው ጴንጤቆስጤዎች (እውነተኛዎቹ፡ የየሐይማኖት ተቋም ሰዎች አይደሉም)፥ ጴንጤቆስጤዎች፡ እርሾን (የየሐይማኖት ተቋማቸውን) የጨመሩት፡ ሞተዋል። ዳሩ ግን ይህ እውነተኛ ቃል ወደ ፊት ይቀጥላል፡ አያችሁ። ልክ ኢየሱስ እንዳለው፡ “በዚያ ቀን፡ በአባቴ ውስጥ እንዳለሁ አባትም በእኔ ውስጥ እንዳለ፡ በእናንተም ውስጥ እንዳለሁ እናንተም በእኔ ውስጥ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ።” ሁሉም ቃሉ ነው!

> ኦህ፡ ያ አስደሳች መገናኘት አይሆንምን! (ልጆቹ በደጃፉ ሲሰበሰቡ።)
> ... አስደሳች መገናኘት!
> እንዴት ያለ አስደሳች ስብሰባ ይሆናል!
> ከአድማስ ማዶ።

285 አሁን፡ ቤተክርስቲያን፡ አሁን እያስተማርን ነው። ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ከዚህ ስትወጡ፡ አሁን ከገለባው ውስጥ መውጣት ጀምሩ፥ ወደ እህሉ እየገባችሁ ነው፡ ዳሩ ግን በልጁ ኅልዎት ውስጥ አርፉ። ባልሁት ላይ፡ አትጨምሩ፥ ካልሁት ላይ፡ አትቀንሱ። ምክንያቱም፡ አብ እንደሰጠኝ መጠን፡ እውነትን እስከማውቀው ድረስ እናገራለሁ። አያችሁ? በእርሱ ላይ አትጨምሩ፡ ያልሁትን ብቻ ተናገሩ።

286 ነገሩ፡ ለሕዝቡ መጥተው ጌታ ኢየሱስን እንዲፈልጉ መንገር ብቻ ነው። ከዚያም ራሳችሁ በኅልዎቱ ውስጥ እርፉ፡ ለእርሱ ፍቅራችሁን ግለጹ፥ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ እወድሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ ልቤን አለስልስልኝ። ርኩሰትን ሁሉና የዓለምን ፍቅር አስወግድልኝ፡ በዚህም ባለው ዓለም በፊትህ በቅድስና እንድኖር አድርገኝ።"

287 ለጸሎት ራሳችንን ዝቅ እናድርግ። አሁን፡ እስቲ እንይ፡ በጸሎት የሚያሰናብተን የተመረጠ ሰው አለን? አለበለዚያ፡ እኔ፡ አደርገዋለሁ። እጅግ ትህትና ይኑራችሁ።

288 ውድ አምላክ ሆይ፡ መንፈሳዊ ምግባችንን ሰላገኘን እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ፡ የቃሉ ቫይታሚን የእግዚአብሔርን ልጆች ሰለሚያሳድግ፡ እናመሰግንሃለን። በእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ላይ እንጂ፡ በየትኛውም ሌላ ዓይነት ባህርይ ላይ ተጽዕኖ አያመጣም። ሰለዚህም እናመሰግንሃለን። አምላክ ሆይ፡ እንድናመሰግንህ ብቻ ሳይሆን፡ በእርሱም እንድንጠቀም ዘንድ፡ እንጸልያለን። ሰለዚህ ነገር እናመሰግንሃለን፡ ዳሩ ግን ጥንካሬውን (በፍቅር) ሰዎችን ማለትም በዚህ ዘመን ያሉትን፥ መንገድ የሳቱትን፡ ኃጢአተኞችን፡ ሴቶችን፡ ወንዶችን፡ ወንዶች ልጆችን፡ ሴቶች ልጆችን በአምላካችን እንዲያምኑ ለማሳመን፡ እንድንጠቀምበት አድርገን።

289 ጌታ ሆይ፡ ሰዎች የሚኖሩበትን የአእምሮ ሁኔታና፡ የጭንቀት ዘመን፡ ሰናይ፡ አእምሯቸውን እያሳታቸው መሆኑን እናያለን፥ መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውንና ቃል የገባውን በትክክል ለመፈጸም፡ ታላላቅ አሰፈሪ ነገሮች በምድር ላይ ይመጣሉ፥ እንደ አንበጣ፡ ጸጉራቸውን የቆረጡትን ሴቶች ለማሰጨነቅ፡ እነርሱም እንደ ሴት ረጅም ጸጉር ይኖራቸዋል። ጌታ ሆይ፡ ባሉበት በዚያ የአእምሮ፡ የቅዠት ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሊያዩዋቸው የሚችሏቸው የተለያዩ፡ አሰፈሪ ትዕይንቶች አሉ፡ ከዚያም ወደ ዓለቶችና ተራሮች ይጮኻሉ። ለውሾችና ለድመቶች እናት የሚሆኑ፡ ዳሩ ግን አንተን የሚያከብሩ ልጆችን የማያሳድጉ ሴቶች አሉ። ልጆችን የሰጠሃቸውና የጸነሷቸው ደግሞ፡ የፈለጉትን እንዲያደርጉ በመንገድ ላይ ይለቋቸዋል። ጌታ ሆይ፡ ወደ መሰቀል በምትሄድበት ጊዜ፡ እንዲህ ማለትህ አያሰደንቅም፡ "በዚያን ጊዜ ዓለቶችና ተራሮች በላያቸው እንዲወድቁ መጮኽ ይጀምራሉ።"

290 ሌላው ነገር ሁሉ እስከዚህ ጊዜ ድረስ በትክክል እየተንቀሳቀሰ መሆኑን እናያለን። መጽሐፍ ቅዱስ የጸና፡ የተረጋገጠ መሆኑን እናያለን። ጌታ ሆይ፡ ያንን፡ አንተን፡ በገዛ ዓይኖቻችን ሰትገለጥ፡ እንደምናይ ሁሉ፡ አንድ ቀን መነጠቅ ይሆናል የዚያንም ቃል መገለጥ እናያለን፡ "የሰው ልጅ በክብር ደመና፡ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ይመጣልና፥ አየር ላይም እርሱን ለመቀበል

እንነጠቃለን።" ያን ጊዜ ይሆናል… አሁን እንሰማዋለን፡ ያን ጊዜ ደግሞ በገዛ ዓይናችን እናየዋለን።

291 ጌታ ሆይ፡ ብቸኛው በተዘጋጀው ሰፍራ፡ በእርሱ ውስጥ እንገኛ። እርሱም መሰዋዕቱ ነው። ስለ እርሱ የሰማነውን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ወደ እግዚአብሔር ቤት እናመጣዋለን። በዚያም መሰዋዕታችን ተቀባይነት ያገኛል ወደ ቤተሰብም እንገባለን፥ ምክንያቱም፡ ገና በዓለም ውስጥ እየባዘንን ሳለን፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንድንሆን ተወስነን ነበርና። አባት ሆይ፡ ስለዚህ ነገር እናመሰግንሃለን። ኦህ፡ እግዚአብሔር ከዓለም እንደ መረጣቸው እውነትን ካገኙ በኋላ፡ ማንም ሰው እንደዚህ ካለው ነገር፡ እንዴት ወደ ኋላ ይመለሳል? እኔ በዳንሁበት ቀን፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጠፍተው ነበር።

292 የሞትኸው በግ ሆይ፡ እንዴት ላመሰግንህ እችላለሁ? ልቤ በፊትህ እንዴት በበቂ ሁኔታ አክብሮት ሊኖረው ይችላል? ውድ አምላክ ሆይ፡ እውነተኛ ሆኜ እንድኖር፡ እርዳኝ። ሕዝቤ እውነተኛ ሆነው እንዲኖሩ እርዳቸው። ጌታ ሆይ፡ ለእያንዳንዳቸው፡ እጸልያለሁ፡ አምላክ ሆይ፡ አንተ በተወሰነ መልኩ፡ እኔ አላውቅም… እንዴት እንደሆነ አላውቅም… ጌታ ሆይ፡ እንዴት እንደምጠይቅ እንኳ፡ አላውቅም፥ ምናልባትም በትክክለኛው መንገድ እየጠየቅሁ ላይሆን ይችላል። ዳሩ ግን ጌታ ሆይ፡ አለማወቄን ይቅር በለኝ፡ ልቤን ብቻ ተመልከት። አባት ሆይ፡ ከእነርሱ መካከል አንዱ እንኳ እንዳይጠፋ፡ አንዱ እንኳ እንዳይጠፋ እጸልያለሁ። እያንዳንዳቸውን፡ የአንተ ይሆኑ ዘንድ፡ እዋጃቸዋለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

እወደዋለሁ፡ እኔ…

እርሱን ከወደዳችሁት፡ እርስ በርሳችሁ ትዋደዳላችሁ። እርስ በርሳችሁ ተጨባበጡ።

65-1128M እግዚአብሔር የመደበው ብቸኛው የማምለኪያ ስፍራ
ላይፍ ተበርናክል
ሽሪቭፖርት, ሉዊዝያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርሰቶሰን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይሰ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግሰ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማሰቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማሰቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org